# በጥላቸው የገዙ!

ከሚሊዩን ዘአማኑኤል

## ሉዓላዊ የቃል ኪዳን ሰነድ (Sovereign Bond)

ካፒታል ገበያ (Capital Market) የአንድ ሃገርና የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠንና ቅልጡፍ ለማድረግ ለኢንቨስትመንት ገንዘብ የሌላቸው በአፋጣኝ ምርታማ ሥራ ለመስራት ብድር ለሚፈልጉ የገንዘብ ፍስቱን ካላቸው ወደ ሌላቸው የብድር ስምምነት በማድረግ የማይጠቀሙበትን ገንዘብ በወለድ በማበደር ለጋራ ኢኮኖሚ እድገትና ለምርታማ ስራ መጠቀም ዋነኛ አላማው ነው። የካፒታል ገበያ በሁለት ይከፈላል አንደኛው የእዳ ዋስትና (Debt Soverine Bond Securities) የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የንብረት ዋስትና (Equity Bilateral loan Securities) የሚሰጥ ነው።በዚህ ሁኔታ ከአንድ አመት የበለጠ የረዥም ግዜ ብድር የገንዘብ አቅርቦት ለማግኘት ይጠቅማል።

የካፒታል ገበያ በሁለት የገበያ ዓይነቶች ይከፈላል።አንደኛው ቦንድ ገበያ (Bond Market)በመባል ይታወቃል። ቦንድ ገበያ የዕዳ ዋስትናን ለማስፈፀሚያነት እንደመሣሪያ እንጠቀምበታለን።ሑለተኛው የስቶክ ገበያ (Stock Market) ይባላል። የስቶክ ገበያ የንብረት ዋስትናን ለማረጋገጥ ይጠቅማል።

በሌላ አገላለፅ ድግሞ የካፒታል ገበያ በአንደኛ ገበያ( Primary Market)አዲስ ቦንድ ወይም አዲስ ስቶክ በማውጣትና ለኢንቨስተሮች በመሸጥ በባንክ አማካኝነት ‹በፁሁፍ›( Underwriting) ቦንድና ስቶክ የምንሸጥበት ዘዴ ነው። ሁለተኛው ገበያ (Secondery Market)አስቀድሞ ባለው በስቶክ ኤክስቼንጅ( Stock exchange)እና በኦቨር ዘ ካውንተር( Over The Counter) ወይም በሌላ መንገድ ለኢንቨስተሮችና ለነጋዴዎች የመሸጥና መግዛት የስቶክ ዝውውር ነው።

የካፒታል ገበያ ቅልጡፍ ለማድረግ ሌክዊዲቲ(Liquidity)የገንዘብ ፍሰት ወይም በአንድ ሀገር ኢኮኖሚው ውስጥ የገንዘብ ፍሰትና ዝውውር ወነኛ ሞተሩ ነው። አንድ ንብረት እንዴት ወደ ገንዘብ ይቀየራል? በምን ያህል ፍጥነት? በኢንደስትሪው ዘርፍ የተሳተፈ ኢንቨስተር ባለሃብት የፋብሪካው ምርቶችን ሸጦ ገንዘብ አግኝቶ ዳግም በገንዘቡ ጥሬእቃና ከውጭ የሚመጡ ግብአቶች ገዝቶበት ዳግም ኢንቨስት በማድረግ ዳግም በማምረት ዳግም ሸጦ ገንዘብ በማግኘት የገንዘብ ፍሰትና ዝውውር አስተማማኝ ሁኔታን መፍጠር ነው። በተመሳሳይ በልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት የተሰማሩ የግል ዘርፍ ባለሃብቶች፣ በሪል ስቴት የተሰማራው ቤቶች ሰርቶ ቤቶቹ በመሸጥ ወደ ገንዘብ እንዴት ይቀይራል፣ ገንዘቡን ሰብስቦ ዳግም ሌሎች ቤቶች ሰርቶ በመሸጥ ወደ ገንዘብ በመቀየር የገንዘብ ፍሰትና ዝውውር ኡደቱን እንዴት አስተማማኝ ያደርጋል ነው ዋናው ቁምነገር። ኢንቨስተሮች ያመረቱትን ምርትና ሸቀጣ ሸቀጦች ካልሸጡና ምርቱ ፋብሪካው ውስጥ ግምጃቤት ከተከማቸ ፋብሪካው የገንዘብ እጥረት ሰለሚያጋጥመው ለዳግም ማምረት አይሰናዳም በዚህም የተነሳ ለሰራተኛ ደሞዝና ለሌሎች ወጭዎችን ለመሸፈን አይችልም። የፋብሪካው የገንዘብ ፍሰትና ዝውውር ኡደት ይቆረጣል ፋብሪካውም ለኪሳራ ይዳረጋል።

የካፒታል ገበያ፣ ዋናው የዓለም ዓቀፍ ሶቨሪን ቦንድ ገበያ የአንድ ሃገርን የኢኮኖሚ እድገት በተለይም የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማፋጠንና የኢንቨስትመንት ገንዘብ ለሌላቸውና ብድር ለሚፈልጉ የገንዘብ በማፈላለግ የገንዘብ ፍስቱን ካላቸው ወደ ሌላቸው የብድር ስምምነት ያደርጋሉ።ኢንቨስተሮች የማይጠቀሙበትን ገንዘብ በወለድ በማበደር ለጋራ ኢኮኖሚ እድገትና ለምርታማ ስራ መጠቀም ዋነኛ አላማው ነው።ኢትዩጵያ ለመጀመሪያ ግዜ በዓለም ዓቀፍ ሶቨሪን ቦንድ ገበያ ለመሳተፍ መንግስት የሶቨሪን ቦንድ ሰነድ፣ የቃል ኪዳን ሰነድ ብድር የመጠየቂያና የማሰባሰቢያ መሣሪያ የቃል ኪዳን ሰነዱን ለአለም አቀፍ ኢንቨስተሮች ለመሸጥ አቅርባል። ማንኛውም መንግስት የተለያዩ የብድር ዓይነቶች በመጠቀም የኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን ይጥራል። መንግስት ሁለት አይነት የብድር ስምምነቶች ያደርጋል አንደኛው የሃገር ውስጥ ብድር(Internal debt) ከሃገር ውስጥ ባንኮች፣ ከብሄራዊ ባንክና ከንግድ ባንክ ወዘተ መንግስት የሚበደረው ገንዘብ ነው። ሁለተኛው የውጭ ብድር (External Debt) ከውጭ ሃገራቶች ጋር መንግስት የብድር ስምምነቶች በማድረግ ገንዘብ ሲበደር ነው ። የውጭ ብድር እንዲሁ ልዩ ልዩ ዓይነቶች ናቸው።አንደኛው፣ በሁለት ሃገራቶች መኃል የሚፈፀም፣ የሁለትዬሽ የብድር ስምምነት (Bilateral loan) በመባል ይታወቃል። ሁለተኛው በአንድ ሃገርና በተለያዩ ሃገራቶች መኃል የሚፈፀም የጋርዬሽ ብድር ስምምነቶች (Multilateral loan) ይባላል። ሦስተኛው ዓይነት የሁለትዬሽና የጋርዬሽ ብድር ስምምነቶች በህብረት ያካትታል።

አራተኛው፣ታሪካዊ ውልደቱ፣ በ1989እኤአ የመጀመሪያው ዓለም ዓቀፍ ቦንድ ገበያ በዓለም ባንክ ሲሰራጭ፣ የቦንድ የገበያ ስርጭት 100 ቢሊዩን ዶላር በመድረስ የውጭ ቦንድ(External bond) ስርጭት ድርሻ 8 በመቶ በ1994እኤአ ለመሆን በቃ። በ1998እኤአ አጠቃላይ የቦንድ ብድር 2000 ቢሊዩን ዶላር በመድረስ በ2000 እጅ ጭማሪ ከ1970እኤአ እድገት በማሳየት፣ በሽህዎች ክንድ አስከነዳ። ለዘህ ዋነኛ እድገቱ የሚሰጠው አስተማማኝ የብድር ዋስትና ሲሆን ጥንታዊውን የባንኮች አሰራር የቦንድ ገበያና ዋስትና ለማስናቅ በቃ።ዓለም ዓቀፍ ቦንድ ገበያ ስርጭት ልማዳዊውን የባንክ የቢዝነስ የብድር አሰጣጥ በታዳጊ ሃገራት ገንዘብ(ብር፣የን፣ሽልንግ ወዘተ) በመሆኑ ከውጭ የካፒታል ጉድስ እቃዎች ለመግዛት አላስቻለም። ዓለም ዓቀፍ ቦንድ ገበያ ግብይይቱ ዶላር፣ፓውንድና ዩሮ ይህን ችግር ቀረፈላቸው። ዓለም ዓቀፍ ቦንድ የሚወጣበት ዋነኛ ምክንያትአስፈላጊው የገንዘብ አቅም በአገር ውስጥ ባለመኖሩና የአገር ውስጥ ቁጠባ ዝቅተኛ መሆኑ ነው። በታዳጊ አገራቶች በቂ የውጭ ምንዛሪ የማፍራት አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ ያንን ለማካካስ ዓለም ዓቀፍ ቦንድ ገበያ ተሳትፈው በውጭ ምንዛሪ ይበደራሉ።

በዓለም ዓቀፍ የቦንድ ገበያ ታዋቂ የሆኑ ብዙ ዓይነቶች የቦንድ ሰነዶች አሉ፣ኮርፖሬት ቦንድ ( Corporate bonds)፣የከተማ አስተዳደር ቦንድ( Municipality bonds)ድራጎን ቦንድ (Dragon Corporate bonds)፣ዩሮ ቦንድ( Eurobonds)ና ሶቨሪን ቦንድ ( Sovereign Bond) የሚባሉ የቃል ኪዳን ሰነድ ብድር መጠየቂያና ማሰባሰቢያ መሣሪያ በመሆን ለአለም አቀፍ ኢንቨስተሮች በመሸጥ ይታወቃሉ፡፡ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን ብቻ እናያለን፡፡

1-ድራጎን ቦንድ(Dragon bonds) የቃል ኪዳን ሰነድ ብድር መጠየቂያና ማሰባሰቢያ መሣሪያ ሲሆን ዋጋውም በዩኤስ አሜሪካን ዶላር ሆኖ በሆንግ ኮንግ ውስጥ ሰነዱ ለኢንቨስተሮችና ለነጋዴዎች ይሸጣል፡፡ ድራጎን ቦንድ በኤሽያ ሃገራቶች ከጃፓን በስተቀር የሚሰራጭ የቃል ኪዳን የብድር ሰነድ ሲሆን ዋና አላማውም፣ በዓለም አቀፍ የቦንድ ገበያ ላይ ብዙ የባህር ማዶ ኢንቨስተሮችን ወደ ኤሽያ ሃገራቶች በመሳብ ይታወቃል፡፡ ድራጎን ቦንድ በአብዛኛው የረዥም ግዜ ብድር ሲሆን በአንፃሩ የአጭር ግዜ ብድር ከ 3 እስከ 5 አመት ይቆያል፡፡

2-ዩሮ ቦንድ( Eurobonds) የቃል ኪዳን ሰነድ ብድር መጠየቂያና ማሰባሰቢያ መሣሪያ ሲሆን ዋጋውም በዩኤስ አሜሪካን ዶላር ሆኖ በተለያዩ አህጉራት የሚወጣ የብድር ሰነድ ነው፡፡

3-ሉዓላዊ የቃል ኪዳን ሰነድ( Sovereign Bond) ብድር የመጠየቂያና የማሰባሰቢያ መሣሪያ በመሆን የአንድ ሃገር መንግስት የሶቨሪን ቦንድ ሰነድ በማዘጋጀት ለአለም አቀፍ ኢንቨስተሮች ሰነዱን በመሸጥና ብድር ለማግኘት በዓለም ዓቀፍ ገበያ ላይ በመሳተፍ የመበደር አቅሞን የምታሰፋበትና እዳዋንም ለመክፈል ብቃት እንዳላት ለዓለም ኢንቨስተሮች ራሶን ለገበያ የምታቀርብበት የብድር ስምምነት ነው፡፡ የሉዓላዊ የቃል ኪዳን ሰነድ፣ዓለም አቀፍ ገበያ ባህሪያቶች እንደሚከተሉት ይገለፃሉ፡- (1ኛ) ብድሩ ለአስር አመታት የሚቆይ መሆኑ (2ኛ) የወለዱ መጠን ከ6 እስከ 7 በመቶ እንደሚሆን ቦንዱን የሸጠው አገር የሚከፍለው ወለድ እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑ፡፡የኢትዬጵያ የሶቨሪን ቦንድ ወለድ በ6.625%x1ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር መሆኑ (3ኛ) የሶቨሪን ቦንድ የሚገዙ አገሮችና ድርጅቶች ቦንዱን የሚገዙት በውጭ ሃገር ገንዘብ በዶለር ወይም ዩሮ ገንዘብ መሆኑ (4ኛ)ሶቨሪን ቦንድ የሚሸጥ አገር ከቦንዱ ሽያጭ የሚያገኘው ገንዘብ ወለዱ የተቀነሰለት ገንዘብ መሆኑ ማለትም አበዳሪዎቹ ወለዱን ቀንሰው (1,000,000,000-66,250,000= 933,750,000 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ብድር የኢትዬጵያ መንግስት እጁ ውስጥ ይገባል፣ የሚከፍለው ደግሞ 1 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ነው፡፡

ሶቨሪን ቦንድ የቃል ኪዳን የብድር ሰነድ በዓለማችን እድሜ ጠገብ የኢንቨስትመንትና የንብረት ሰነድ ነው፡፡ብሄራዊ መንግስታት ሉዓላዊ የቃል ኪዳን የብድር ሰነድ ሲያወጡ ክፍለ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ዛሬ የሶቨሪን ቦንድ ዓለም አቀፍ ገበያ ዋናው የብድር ማግኛ የመሰረት ድንጋይ በመሆን በብዙ ኢንስቲቲዩሽናል ኢንቨስትመንት ተቆምና ድርጅቶች የተያዘ ገንዘብ በመሆን እንዲሁም፣በብዙ ግለሰብ ኢንቨስተሮች ታዋቂነት እያገኘ የመጣ የብድር ሰነድ ለመሆን በቅቶል፡፡ የሶቨሪን ቦንድ እዳ በሁለት ይከፈላል፡፡ አንደኛው የሶቨሪን ቦንድ ሰነድ የሚወጣው በአደጉ ሃገራቶች ለምሳሌ ጀርመን፣ ሲዊዘርላንድ፣ካናዳ በመሳሰሉት ሃገራቶች ወጥቶ የሚሰራጭ የቃል ኪዳን ሰነድ ሲሆን፣ከፍተኛ የወለድ ተመን ሲኖረው ሰነዱ በጣም አስተማማኝ ዋስትና ያለው ሲሆን በአንፃሩ የሚቀርበው የብድር ገንዘብ መጠን አነስተኛ ነው፡፡ሁለተኛው የሶቨሪን ቦንድ ሰነድ የሚወጣው በታዳጊ ሃገራቶች ወይም ዓለም አቀፍ የቦንድ ገበያ እየገቡ ያሉ ሃገራት የሚወጣ የቃል ኪዳን የብድር ሰነድ ነው፡፡ዝቅተኛ የወለድ ተመን ሲኖረው ሰነዱ በጣም የወደቀ ዋስትና ያለው ነው፡፡ ዋና ምክንያቱም የቃል ኪዳን የብድር ሰነድ አስተማማኝ ያልሆነና ቁሻሻ ቦንድ ( rated as junk.) ሲባል፣ በአንፃሩ የሚቀርበው የብድር ገንዘብ መጠን ከፍተኛ ነው፡፡ ታዳጊ ሀገራት ሰነድ በመሸጥ ብድር መበደር ለመቀጠል እዳቸውን በወቅቱ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ አንዳንድ ታዳጊ ሃገራት ብድር የመበደር ብቃት ባይኖራቸው አሊያም እዳቸውን መክፈል ባይችሉ እንኳን በዓለም አቀፍ የቦንድ ገበያ የሚያሰራጩት የሶቨሪን ቦንድ፣ለአለም ገበያ በሚሸጡበት ግዜ ከሃገራቸው ውስጥ ከሚያሰራጩት ቦንድና ስቶክ የበለጠ ተቀባይነትና ዋስትና አለው፡፡

መንግስታት ዕዳቸውን የመክፈል ፍላጎት በሚከተሉት የፖለቲካ ስርዓትና የመንግስታዊ የአመራር ብቃት ላይ ይመሰረታል፡፡ አንድ መንግስት የመክፈል አቅም እያለው፣እዳውን የመክፈል ፍላጉት ላይኖረው ይችላል ፡፡ብዙ ግዜ የመንግስት ለውጥ በሚከሰት ግዜ ለምሳሌ ሶቭየት ህብረት የ5 ቢሊዩን ዶላር ደርግ መሣሪያ የገዛበትን፣ለሃገራችን ዕዳ ሰርዛለች፡፡ ይህ ሁኔታ የፖለቲካ አለመረጋጋት ባለባቸው አገራትም ይከሰታል፡፡የሃገራት ፖለቲካ አለመረጋጋት አማካሪዎች ለኢንቨስተሮች የሶቨሪን ቦንድ የብድር ሰነድ መግዛትና አለመግዛት ሁኔታን ይወስናሉ፡፡የሃገራቶችን የብድር የመክፈል አቅምና አመላለስ ብቃት በማጥናት ደረጃ በማውጣት የሚታወቁ ኩባንያዎች ፊች፣ሙዲስ፣ኤስኤንድፒና እንዲሁም ትሬዲንግ ኢኮኖሚክስ የተባሉ ኩባንያዎች የየአገሮችን ብድር ዕዳና የመመለስ አቅምን በመለካት ይታወቃሉ፡፡ የተለያዩ ደረጃዋች ሲኖሩ፣ሦስት ኤ/ትሪፕል ኤ (3A)፣ድርብ ኤ(2A) ፣ነጠላ ኤ(1A) ፣ሦስት ቢ/ትሪፕል ቢ(3B) ፣ድርብ ቢ (2B) ፣ነጠላ ቢ(1B) የሚል የደረጃ ድልድል የሚወጡ ሲሆን፣ በተለይ በኢንቨስትመንት ረገድ ለአገሮችም ሆነ ለኩባንያዎች የሚሰጡት ሦስት ደረጃ የሚያገኙ አገሮችና ለኩባንያዎች ከፍተኛ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያስችልና በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ነው፡፡ በፓሪስና በለንደን መቀመጫውን ያደረገው ፊች(Fitch) የእዳ ደረጃ ለኪ ኩባንያ ዓለም አቀፍ ተቆማት የሃገራትን ብድር የመክፈል ፍላጎትና ዐቅም ወይም ችሎታ በማጣራት በደረጃ ይመድባሉ፣በዚህም መሠረት ኢትዩጵያ የረዝም ጊዜ የውጭና የአገር ውስጥ እዳዋን/ ብድሮን መነሻ በማድረግ መጨረሻውን፣የነጠላ ቢ(1B) ደረጃ አግኝታለች፡፡ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት በመንግስታዊ ልማት ድርጅቶች ብድርን ከመንግስት ብድር ነጥሎ በማሳየቱና በማጭበርበር የተገኘ ውጤት እንደሆነ ልብ ይበሉ፡፡ በዚህም ደረጃቸው ከዓለም አቀፍ የቦንድ ገበያ፣ የሶቨሪን ቦንድ ብድር የማግኘት ችሎታቸው ይመዘናል፡፡ ተበዳሪው መንግስት የሸጠውን የሶቨሪን ቦንድ ዕዳ መክፈል ካልቻለ በዚህ ግዜ የቦንድ ሰነድ የገዛው ወይም የቦንድ ያገዥ (bondholders) የወለድ ክፍያና ዋናውን ገንዘብ በተባለው ግዜ መውስድ አይችልም፡፡ በዚህ ግዜ የቦንድ ያገዙ ከመንግስት ጋር የተለያዩ ስምምነቶች ያደርጋል፡፡ መንግስት እዳውን በተባለው የግዜ ሠሌዳ መክፈል ባልቻለ ግዜ፣ከቦንድ ያገዙ ጋር፣የዕዳ ሽግሽግ (debt restructuring) ለማድረግ ይስማማል፡፡ ስምምነቱም የሚያካትታቸው ዝቅተኛ የወለድ ተመን፣የብድሩን አመት ማራዘምና ዋናውን ገንዘብ መቀነስ በመሳሰሉት ላይ አዲስ ስምምነት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ስምምነት የቦንድ ያገዙ ሲጎዳ መንግስት ይጠቅማል፡፡ ሌላው የቦንድ ያገዙን የሚጎዳ ነገር ደግሞ የዋጋ ግሽበት(inflation) የቦንድ ገኘው ዋና ገንዘብና የወለድ ክፍያ እሴት በመቀነስ ይጎዳዋል ማለትም የገንዘቡ የመግዛት አቅም ከበፊት ግዜ ዋጋው ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የቦንድ ያገዙ ይጎዳዋል፡፡

ሶቨሪን ቦንድ የቃል ኪዳን የብድር ሰነድ አደጋን ለመከላከል የቦንድ ገዥዎች የሚያደርጉት መከላከያ ዘዴዎች መኃል አንደኛው ጥናት ማድረግ የሃገሪቱ መንግስት ዕዳ የመክፈል አቅምን ፍላጎት ያስጠናሉ፡፡ ሁለተኛ ዓለም አቀፍ ተቆማት የሃገራትን ብድር የመክፈል ፍላጎትና ዐቅም ወይም ችሎታ በማጣራት የብድር ደረጃ ይሠጣሉ ያን መረጃ ከፊች(Fitch) ይጠይቃሉ፡፡ ሦስተኛ ደግሞ የሶስተኛ ፓርቲ ጥናትን በመጠቀም ለምሳሌ የኢኮኖሚ ኢንቴሌጀንስ ክፍል ወይም ሲአይኤ የዓለም ፌስቡክ (CIA World Factbook) መረጃ በመጠየቅ የሶቨሪን ቦንድ አውጭውን ሃገር መንግስት የብድር መረጃ ያጠናሉ፡፡ ሶቨሪን ቦንድ የቦንድ ገዥዎች ሌላ አደጋ መከላከያ ዘዴ ከአንድ አገር ብቻ ቦንድ ግዥ ከማድረግ ይልቅ፣ ከተለያዩ ሃገራት መንግስታት ሶቨሪን ቦንድ በመግዛት ኢንቨስት በመድረግ ራሳቸውን ከአደጋ ይጠብቃሉ፡፡ ሌላው የቦንድ ገዥዎች በተለያዩ ሃገራቶች ገንዘብ ዩኤስ ዶላር፣ ዩሮና ፓውንድ ሶቨሪን ቦንድ በመግዛት አደጋውን ይከላከላሉ፡፡

የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት የነዚህን ‹መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች› እዳ የኢትዮጵያ መንግስት እዳ እንዳልሆነና በብድሩም መንግስት ተጠያቂም እንዳአይደለ ለዓለምአቀፍ የገንዘብ ተቆም ማረጋገጡ ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ የህወሃት መንግስትና የአለም ባንክና አይኤም ኤፍ ጋር ምንም ስምምነት ሳይደርሱ ነው ወደ ዓለም ዓቀፍ ሶቨሪን ቦንድ ገበያ፣ሶቨሪን ቦንድ ሰነድ ብድር የመጠየቂያና የማሰባሰቢያ የተሄደው፡፡ ሃገሪቱ ባለባት የእዳ ጫና ምክንያት ምንም አበዳሪ በመጥፋቱ የተነሳና የተጀመሩትን የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ለማሰጨረስ የውጭ ምንዛሪ የሚያስፈልጋቸውን ማሽነሪዎችና ዕቃዎች ገዝቶ ለማስገባት ዶላር፣ ዩሮና ፓውንድ ሃገሪቶ ስለሌላት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የብድር አቆማዳውን አንጠልጥሎና የቃል ኪዳን ሰነድ አዘጋጅቶ ለመሸጥና፣ብድር ለመጠየቅ ለክሬዲት ስዊስ፣በርክሌ፣ጄፒ ሞርጋንና ለአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ የፋይናንስ ተቆማት በማቅረብ ብድር ማግኘት የቻለው፡፡ ኢትዮጵያ ከሶቨሪን ቦንድ ሰነድ፣ብድር አንድ ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ወይም (20,000,000,000 ቢሊዩን ብር) ብድር ለአስር አመት በ6.625 በመቶ ወለድ በ6.625%x1ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር(66,250,000 ዩኤስ ዶላር) በዓመት ትከፍላለች፡፡ በ2007 እኢአ የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት ባጀት 178.6 ቢሊዩን ብር ሆኖ በፓርላማ እንደፀደቀ ሲገለፅ ከዚህም ውስጥ የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ 8,190, 000,000 ቢሊዩን ብር (409,500,000 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር) እንደሆነ በዚህም የብድር ስሌት ኢትዩጵያ ለሶቨሪን ቦንድ ብድር የሃገሪቱ አጠቃላይ የውጭ ዕዳ ክፍያ 475,750,000 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ወይም 9,515,000,000 ቢሊዩን ብር በዓመት መክፈል ይጠበቅባታል ማለት ነው፡፡ የመንግስታዊ ልማት ድርጅቶች የውጭ ዕዳ ክፍያ ሳይታከልበት፡፡

የሶቨሪን ቦንድ፣የብድር ጫና ስጋት (**Risks from Sovereign Debt**) የአንድ መንግስት የሶቨሪን ቦንድ ገበያ የመክፈል አቅም የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ጥንካሬን ያሳያል( A government's ability to pay is a function of its economic position.)፡-ከዚህ ቀጥለን ደግሞ፣ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት የሶቨሪን ቦንድ የመክፈል አቅም ደካማ መሆን የሚያመላክተን፣ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ዕዳውን የመሸከምና የመክፈል አቅም ደካማ መሆንን በስታስቲካል ማስረጃ እናሳያለን፡፡

1-ሃገሪቱ ደካማ ኢኮኖሚ እንዳላት (a country with a weak economy) መረጃው፣አመታዊ አጠቃላይ ብሄራዊ የሃገር ውስጥ ምርት በ1990እኤአ 12 ቢሊዩን ዶላር፣በ2010እኤአ 30 ቢሊዩን ዶላር፣በ2013እኤአ 46 ቢሊዩን ዶለር የነበረ ሲሆን በዚሁ አመታት የህዝቡ የነፍስ ወከፍ ገቢ(257፣398፣ 350፣418 ዶለር) እንደነበረ ሠንጠረዡ ከታች ያመላክታል፡፡ የሃገሪቱ አመታዊ አጠቃላይ ብሄራዊ የሃገር ውስጥ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ፣ከሳህራ በታች ባሉ ሃገራቶች ዝቅተኛው መሆኑ ከሠንጠረዡ መመልከት ይቻላል፡፡

| Year | Gross Domestic Product Birr(Millions) | GDP USD(Millions) | GDP(Birr) Per capita | GDP(USD) Per capita | US Dollar Exchange |
|---|---|---|---|---|---|
| 1980 | 14,665 | 7,119 | 391.4 | 190 | 2.06 Birr |
| 1985 | 19,476 | 9,454 | 453.2 | 220 | 2.06 Birr |
| 1990 | 25,011 | 12,141 | 529.42 | 257 | 2.06 Birr |
| 1995 | 47,560 | 8,088 | 870.24 | 148 | 5.88 Birr |
| 2000 | 64,398 | 7,902 | 1010.6 | 124 | 8.15 Birr |
| 2005 | 106,473 | 12,309 | 1461.85 | 169 | 8.65 Birr |
| 2006 | 131,672 | 15,694 | 1694.78 | 202 | 8.39 Birr |
| 2007 | 171,834 | 19,242 | 2259.29 | 253 | 8.93 Birr |
| 2008 | 245,973 | 25,437 | 3220.11 | 333 | 9.67 Birr |
| 2009 | 353,455 (est) | 28,527 | 5179.02 | 418(est) | 12.39 Birr |
| 2010 | 403,100(est) | 30,240 | 5305.34 | 398(est) | 13.33 Birr |

"The Federal Democratic Republic of Ethiopia: Selected Issues Series", International Monetary Fund Country Report No. 08/259, pp. 35f (Retrieved 4 February 2009)- The current GDP (USD) per capita of Ethiopia shrank by 43% in the 1990s.

The following table displays the trend of Ethiopia's gross domestic product at market prices, according to estimates by the International Monetary Fund with figures in millions of Ethiopian Birr.

Ethiopia's Avereage Trade deficit (in million Birr), 2005-2009

| Year | Export Value Birr (Million) | Import Value Birr (Million) | Trade deficit Birr (Million) | Trade deficit USAD(Million) |
|---|---|---|---|---|
| 2005 | 7,698 | 32,613 | -24,915 | - |
| 2006 | 8,786 | 39,890 | -31,104 | -3.08 |
| 2007 | 10,706 | 49,180 | -38,474 | -3.87 |
| 2008 | 14,946 | 79,510 | -64,564 | -5.65 |
| 2009 | 17,733 | 90,556 | -72,823 | -5.28 |
| 5-years Average | 11,974 | 58350 | -46,376 | |

Source: Ethiopian Revenue and Customs Authority

ከሠንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው በ2005 እኤአ የኢትዩጵያ የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ 7,698,000 ቢሊዩን ብር የሚያወጣ የአገር ውስጥ ምርት ወደ ውጭ ሃገራት ተልኮል፡፡ በአንፃሩም 32,613,000 ቢሊዩን ብር የሚያወጣ የውጭ ሃገር ምርት ወደ ሃገራችን ገብቶል፡፡ በዚህም የተነሳ -24,915,000 ቢሊዩን ብር የንግድ ኪሳራ (Trade deficit) ተመዝግቦል፡፡የንግድ ኪሳራው እየጨመረ በመሄድ በ2006(-31,104)፣በ2007(-38,474)፣በ2008(-64,564)፣በ2009(-72,823) ቢሊዩን ብር የንግድ ኪሳራ እንደተመዘገበ የኢትዩጵያ ገቢዋችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዘግቦል፡፡

በ2012/13 እኤአ አማካይ የውጭ ምንዛሪ ተመን አንድ ዩኤስ አሜሪካ ዶለር በ18.6518 የኢትዩጵያ ብር የዋጋ ተመን ስለነበር በዛ ተሰልቶ የተቀየረ ነው፡፡ በዚህ ዓመት የኢትዩጵያ የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ 64,247,293,188 ቢሊዩን ብር (3,444,562,626 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር) የሚያወጣ የአገር ውስጥ ምርት ወደ ውጭ ሃገራት ተልኮል፡፡ ከባህር ማዶ ሀገራትም 176,697,900,620 ቢሊዩን ብር (9,473,503,931 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር) የሚያወጣ የውጭ ሃገር ምርት ወደ ሀገራችን ገብቶል፡፡ የንግድ ሚዛኑም ሲሰላ፣ ከገቢ ንግድ ላይ ወጭ ንግድ ሲቀነስ -112,450,607,432 ቢሊዩን ብር (-6,028,941,305 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር) የንግድ ኪሳራ (Trade deficit) ተመዝግቦል፡፡ ይህንን የንግድ ኪሳራ በየዓመቱ መንግስት የሚሸፍነው ከውጭ ብድር ነው፡፡ ለምሳሌ፤ በ2012/13 የነዳጅና ዉጤቶች 1,466,114,603 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር በገቢ ንግድ ወደሃገር ተከፍሎ ገብቶል፡፡ በ2014/15 እኤአ ሦስት የውጭ ባንኮች(ኢንተርናሽናል ፋይናንሻል ኮርፖሬሽን(አይኤፍሲ)፣የፈረንሳዩ ኢንቨስትመንት ናቲክሲስ ባንክና ስታንደርድ ባንክ ግሩፕ) ለኢትዩጵያ ዓመታዊ የነዳጅ ወጪ የሚውል 500 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የብድር አገልግሎት ሰኔ 2014እኤአ ብድር ለመስጠት ተስማምተዋል፡፡የአገራችን የዉጭ ብድርና የዉጭ ንግድ ገቢ መጣኔ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ፡፡ አጠቃላይ የውጭ ብድር 31.5 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ይህ ማለት ደግሞ ምርታችንን ለአለም ገበያ አቅርበን የምናገኘዉ የዉጭ ምንዛሪ ከ2.5 እስከ 3 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ሲገመት ከዉጭ አገር ዕቃ ሊገዛልን ቀርቶ የተበደርነዉን ብድር ወለዱንም መክፈል አይችልም ማለት ነዉ፡፡ ‘‘Export revenues have more than doubled since 2004, reaching US$ 2 billion in 2010. The share of non-traditional exports, notably flowers, gold, meat and leather products increased to 74.6% in 2010 from 60%. Over the same period imports, especially for capital goods, grew rapidly (on average by about 27.4% per annum). FDI and remittances have also witnessed strong growth. Within a period of six years,FDI increased eightfold to reach US$ 950 million in 2010. Remittances grew, on average, by 34% per annum to reach US$ 2.2 billion. However, the current account deficits remained high, at an average of 6% of GDP, due to the fact that Ethiopia is an importer of oil and capital goods’’**Source:-FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIACOUNTRY STRATEGY PAPER 2011-2015,** *April 2011*

2- ኢትዩጵያ ከፍተኛ የዕዳ ጫና( high debt burden,) ያለባትንና ብድሯን የማስተዳደርና፣መቆጣጠር አቅም ከሌላቸው ደሃ ሃገራት ትመደባለች መረጃው፣ከሳህራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት የውጭ ብድር ቀውስ መሠረት ቀውሱ በጣም የተወሳሰበ የብዙ መሰረታዊ ነገሮች ድምር ውጤት መሆኑ ይታመናል፡፡ አንዳንዶቹ ነገሮች ለተበዳሪ/ባለእዳ አገሩ ውጭያዊ ተፅእኖ አላቸው፡፡ ለሌሎቹ ሃገራት ደግሞ ቀጥተኛ ተፅእኖ ያላቸው የተሳሳቱ የመንግስት ፖሊሲዎች የመሰረት ድንጋይ ሲሆኑ የውጭ ብድር ተጽፅኖ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ያበረከተውን ይቃኛል፡፡ ኢትዮጵያ በዲሴንበር 6/2011እኤአ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ዘመነ መንግስት የቻይና አስመጭና ላኪ ባንክ( Chinese Export and Import Bank) በኩል የቻይና መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት 11.4 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር(272.2 ቢሊዩን ብር) እንዳበደሩ በግዜው ተገልጸዋል፡፡ከሌሎች ሃገራትና አለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር 8.6 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የውጭ ዕዳ አለብን፡፡እንዲሁም በኢትዮጵያ የሚገኙ ‹መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች› ማለትም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል፣የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት፣ የብረታ ብረትና ኢንደስትሪያል ኮርፖሬሽን የመሳሰሉ ድርጅቶች በራሳቸው የሚያደርጉት የውጭ ብድር 11.5 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር በላይ ይገመታል፡፡በአጠቃላይ 31.5 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የውጭ ብድር እንዳለባት ይገመታል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገራቶች ላይ የተቀለለው የውጭ ብድርና ዕዳ ከፈላ ለአገራቱ የኢኮኖሚ እድገትና ብልፅግና እንቅፋት መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም መሠረት እንደ የዓለም ባንክ ምደባ መሠረት ሃገሪቱ የተቀለለ እዳ የተጫነበት ኢኮኖሚ ትመራለች፡፡ አገራችን ከፍተኛ እዳ ከተቀለለባቸው ዝቅተና ገቢ ያላቸው አገራት መኃል አንዶ መሆኖ ይታወቃል፡፡ በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ባለው ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር በመጠን፣ ትልቅ ለውጥ ታይቶበታል፡፡ በ1975 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 343.7 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 14% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ በ1991 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 9.1 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 214% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ በጁን 30 1999 ይሄ አሃዝ 10.2 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር ከፍ ብሎል፡፡በ2013 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 16.11ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 46 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር 285.5% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ የውጭ ብድር ፋታ የተሰጣቸው የእድገት ተነሳሽነታቸውና አሠራር መሠረት ከፍተኛ እዳ የተቀለለባቸው ደሃ አገራቶች መኃል የኢትዮጵያ አጠቃላይ የውጭ ብድር 30 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር ወይም በኢትዮጵያ ብር (559,554,000,000 ቢሊዩን ብር) እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ በ2012/13 እኤአ አማካይ የውጭ ምንዛሪ ተመን አንድ ዩኤስ አሜሪካ ዶለር በ18.6518 የኢትዩጵያ ብር የዋጋ ተመን ስለነበር በዛ ተሰልቶ የተቀየረ ነው፡፡በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዕዳና($30 ቢሊዩን ተሰልቶ) አጠቃላይ አገራዊ ምርት (GDP) መጧኔ ቁጥሩ ከፍተኛ መሆኑ ይስተዋላል፡፡ይህ ማለት ኢትዮጵያ የተቀለለባት የውጭ ዕዳ 153 በመቶ የ2013 ዓመታዊ አጠቃላይ ብሄራዊ ምርት (46 ቢሊዩን ዶላር) መሆኑን ያሳያል፡፡ ‘‘According to the 2010 Debt Sustainability Analysis (DSA) undertaken by the IMF and World Bank, Ethiopia‘s external debt stock is rising largely due to the surge in public enterprises external borrowing.4 The DSA indicate that the Present Value of debt to GDP and Debt toExports are projected to rise from 13.5% and 119.1% in 2010 to 18.3% and 129% respectively in 2011, before declining in subsequent years. While external debt indicators are still within the thresholds and Ethiopia‘s risk of debt distress has been lowered from moderate to low, the situation will require close monitoring, especially public enterprise borrowing.’’ [4]See IMF, 2010, Article IV Consultation and 1st Review of Arrangement under ESF, Washington DC.

3- የመግዛት አቅም የሌለው ገንዘብና የሚዋዥቅ የውጭ ምንዛሪ ተመን( weak or volatile currency)መረጃ መሠረት፣ ከ1980 እኤአ እስከ 2014እኤአ አንድ ዩኤስ ዶላር ወደ ስንት የኢትዩጵያ ብር እየተተመነ፤ማለትም የብር የመግዛት አቅም ቅነሳ (*devaluation*) እያደረገ እንደመጣና ቅናሹ በመቶኛ ተሰልቶም በሰንጠረዡ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

| Year | 1980 | 1985 | 1990 | 1992 | 1995 | 2000 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| US D$=Birr | 2.07 | 2.07 | 2.07 | 5.00 | 5.88 | 8.15 | 8.65 | 8.39 | 8.93 |
| *Depreciation by %* | 0 | 0 | 0 | 241.5 | 117.6 | 138.6 | 106.1 | -97 | 106.4 |
| Inflation rates *by %* | | | | | | | 9.95%, | 12.20%, | 17.25%, |

| Year | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| US D$=Birr | 9.67 | 12.39 | 13.33 | 14.06 | 18.6518 | 19.6511 | 19.8476 | 21.8324 |
| *Depreciation by %* | 108.3 | 128.1 | 107.6 | 105.5 | 132.7 | 105.4 | 101 | 1 10 |
| Inflation rates *by %* | 43.80%, | 10.57%, | 8.12% | 33.00%, | 23.33% | 8.07%. | | |

"Annual inflation rates in Ethiopia from 2005 to 2013, respectively, were 9.95%, 12.20%, 17.25%, 43.80%, 10.57%, 8.12%, 33.00%, 23.33% and 8.07%. The reader can observe from this that the exchange rate has not been coping with the country's inflation rates."**The Devaluation of the Birr: A Layman's Guide, Part 2:** By Seid Hassan, Murray State University; August 1, 2014

በ2014 እኤአ ኢትዩጵያ የአንድ ቢሊዩን ዶላር ብድር ተበድራለች፣በአሁኑ ወቅት ባለው የምንዛሬ ተመን ምጣኔ መሰረት 20 ቢሊዩን ብር ነው፡፡ የኢትዩጵያ ብር (**Devaluation**) የመግዝት አቅሙ ቢቀንስ፣ማለትም የምንዛሪው ተመን ወደ 22 ብር ከፍ ቢል ተመሳሳይ መጠን ላለው ብርድ(1ቢሊዩን ዶላር ብድር) የሚከፈለው 22 ቢሊዩን ብር ይሆናል ማለት ነው፡፡ የአለም ባንክና አይኤም ኤፍ **የኢትዩጵያ ብር እንዲቀንስ፤ማለትም የብር የመግዛት አቅም ቅነሳ** (*devaluation*) **እንዲያደርግ ደጋግመው አሳስበዋል የወደፊት እጣ ፈንታችን ምን ይሆን? የኢትዩጵያ ብር የውጭ ምንዛሪ ተመኑ ይቀንሳል አይቀንስም? ወደፊት እናየዋለን፡፡**

4- **ደካማ የታክስና የቀረጥ መሰብሰብ ችሎታ** (little ability to collect taxes) በኢትዩጵያ የታክስና ቀረጥ ገቢ በአማካይ 27.3 በመቶ እየጨመረ ሄዶ፣ በ2010 እኤአ 43.3 ቢሊዩን ብር ደርሶል፡፡ሆኖም ከአመታዊ አጠቃላይ ብሄራዊ ምርት የታክስና ቀረጥ ገቢ 11 በመቶ ብቻ ድርሻ ስላለው **ደካማ የታክስና የቀረጥ መሰብሰብ ችሎታ እንዳለው ይታወቃል፡፡የወያኔ አገዛዝ የብድር ዕዳና አገዛዙ አገር ዉስጥ በግብር መልክ የሚሰበስበዉ ገቢ መጣኔ እጅግ በጣም ከፍተኛና ፍትሃዊ ባለመሆኑ የተነሳ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስተሮች በኪሳራ እየተዳረጉ በመዘጋት ላይ ሲገኙ ‹የመንግስታዊ ልማት ድርጅቶች›ና ኢፈርት፣ ሜቴክ፣እንዲሁም የህወሃት የጡት አባት ሜድሮክ ሞኖፖሊ ካንፓኒዎች የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡**

''GoE's adjustment efforts have paid off, with macroeconomic stability largely restored. Domestic borrowing has been contained within 1.5% of GDP. Since 2004, when the current growth episode started, tax revenues increased, on average, by 27.3% annually reaching ETB 43.3 billion in 2010—although still only about 11% of GDP.''

**Source:-FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIACOUNTRY STRATEGY PAPER 2011-2015,** *April 2011*

5- **አስተማማኝ የስነ ህዝብ/ሕዝበ ፅንፍ መረጃ** (positive demographics will likely have the ability to pay back its debt.)**ካላት የሶቨሪን ቦንድ ብድሯን የመክፈል አቅም አይኖራትም፡፡ የሃገሪቱ የብድር የመክፈል አቅምና ችሎታዋ ደግሞ በጠንካራ የብድር የመክፈል ደረጃ በዓለም የብድር ደረጃ መዳቢ ኤጀንሲዎች የተሰጣት ምደባ ይንፀባረቃል፡፡**(This ability will usually be reflected in a strong credit rating by the major ratings agencies.) **መንግስት የህዝብ አመኔታ የለውም፣ ዴሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መኖር፣የስራ አጥነት፣በእቅድ ላይ ያልተመሠረተ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የህዳሴው ግድብ፣ቴሌኮም፣ የኤሌትሪክ ኃይል፣የባቡርና መንገድ፣የስኳር ፋብሪካ፣ወዘተ ከፍተኛ የእዳ ጫና አስከትሎል፡፡**

6- **የተለያዩ መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች፣ የኢትዩጵያ አየር መንገድ፣የኢትዩጵያ ቴሌኮም፣የኢትዩጵያ ንግድ ባንክ፣ የኢትዩጵያ ኤሌትሪክ ኃይል፣የኢትዩጵያ መጎጎዣ መርከብ ድርጅት፣ የብታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የመሳሰሉት ድርጅቶች በግላቸው የሚበደሩት የውጭ ብድሮች** 11.5 **ቢሊዬን ዩኤስ ዶለር ይገመታል፡፡ ፊች ኩባንያ የእዳ ደረጃ ለኪ ኩባንያ በኢትዩጵያ መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች**(SoE) **እዳ** 25 **በመቶ** በ2013 **እኤአ አመታዊ አጠቃላይ ብሄራዊ ምርት** 46 **ቢሊዩን የነበረ ሲሆን** 11,500,000,000 **ቢሊዬን ዩኤስ ዶለር የውጭ ብድር እንዳለባቸው ገልፆል፡፡**‹‹Fitch estimates that total State –owned enterprises(SoE) debt amounted to at least 25 per cent of GPD at end-June 2013, doubling consolidated total public debt.››**የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት አጠቃላይ የውጭ ብድር** 31.5 **እና የሶቨሪን ቦንድ የመክፈል አቅም ደካማ መሆን የሚያመላክተን፣የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ዕዳውን የመሸከምና የመክፈል አቅም ደካማ መሆንን ያሳያል፡፡**

**የኢትዬጵያ አየር መንገድ፣አይሮፕላኖቹን እያስያዙ ከተለያዩ ባንኮች የሚያደርጎቸውን የውጭ ብድሮች ቀጥለን እንመልከት፡፡** በ2008 **እኤአ ስምንት ቦንባርዲየር ኪው** 400 **አይሮፕላኖች** 242 **ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር፣**በ2010**እኤአ አስር ቦይንግ** 737-800 **አይሮፕላኖች** 767 **ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ዋጋ ለመግዛት ተስማምተዋል፣ የቻይናው ኤክፖርት ኢንፖርት ባንክ የ**1.6 **ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ለአስር ቦይንግ ድሪም ላይነርስ አበድሮል፡፡** በ2011 **እኤአ አራት ቦይንግ** 777**ኤፍ አይሮፕላኖች በ**1.1 **ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ለመግዛት ስምምነት ተፈፅሞል፡፡** በ2012 **እኤአ አምስት ኪው** 400 **አይሮፕላኖች** 160 **ሚሊዩን ዩኤስ ዶለርና ተጨማሪ አንድ ቦይንግ** 777-200**ኤልአር አይሮፕላን** 276 **ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር ለመግዛት ስምምነት ተደርጎል፡፡ በተለያየ ግዜትም የተገዙት አይሮፕላኖች ወደ አገር ውስጥ ገብተዋል፡፡**በ2013 **እኤአ ኤር ሊዝ ኮርፖሬሽንና የኢትዬጵያ አየር መንገድ ሁለት ቦይንግ** 777-300 **ኢአር አይሮፕላኖች ለመከራየት ተስማምተው፣ የቻይናው ኤክፖርት ኢንፖርት ባንክ የ**130 **ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ለኢትዬጵያ አየር መንገድ ብድር አበደረ፡፡** በ2014 **እኤአ የኢትዬጵያ አየር መንገድ** 20 **ቦይንግ** 737 **ማክስ** 8 **አይሮፕላኖች የ**2.1 **ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ከዩኤስ አቪየሽን ጋር ስምምነት አደርገዋል፡፡ በተጨማሪም አስራአምስት** 737 **ማክስ** 8 **ነዳጅ ቆጣቢ አይሮፕላኖች ለመግዛት ስምምነት ፈፅመዋል፡፡በአጠቃላይ ከ** 2008**እኤአ እስከ** 2014**እኤአ የኢህአዲግ መንግስትና የኢትዬጵያ አየር መንገድ ድርጅት** 5,608,000, 000 **ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ወይም** (104,599,294,400 **ቢሊዩን ብር**) **አይሮፕላኖች ለመግዛት የውጭ ብድር ተበድሮል፡፡ የቻይናው ኤክፖርት ኢንፖርት ባንክ አይሮፕላኖቹን** 1,730,000,000 **ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ወይም** (32,267,614,000 **ቢሊዩን ብር**) **በማበደር የአንበሳውን ድርሻ በመያዝ የኢትዬጵያ አየር መንገድ አይሮፕላኖች በወለድ አግድ** collatoral **በመያዝ እንደሚያበድር ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ የኢትዬጵያ አየር መንገድ Total assets** (**አጠቃላይ ንብረት**) 26.368 **ቢሊዩን ብር**(1,413,697,338 **ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር**)**በ** 2012**እኤአ ነበር፡፡ በእዳ ብዛትም የኢትዬቻይና አየር መንገድ እንዳይባል ያሰጋዋል፡፡የኢህአዲግ መንግስትና የኢትዬጵያ አየር መንገድ ድርጅት የውጭ ብድር በተመለከተ ብቻ የቀረበ ሲሆን፣ የአገር ውስጥ ብድር ከተለያዩ ባንኮች የተበደሩትን እንደማይጨምር አንባቢ ሊገነዘብ ይገባል፡፡** 2012**እኤአ የኢትዩጳያ የአገር ውስጥ ብድር** 45.5 **ፐርሰንት ከዓመታዊ አጠቃላይን ብሔራዊ ምርት የነበረ ሲሆን የውጭ ብድር** 10 **ፐርሰንት ከዓመታዊ አጠቃላይን ብሔራዊ ምርት የያዘ ነበር፡፡**

የኢትዮጵያ ስካY ኮርፖሬሽን የወንጂ ሸዋ ፣የመተሃና የፊንጫ ስካY ፋብሪካዎችን ጠቅልሎ በመያዝ በበላይነት እያስተዳደረ ይገኛል፡፡ኮርፖሬሽኑ በደቡብ ክልል ሰባት፣ በአማራ ክልል ሦስት፣ እንዲሁም በትግራይ ክልል አንድ(የአፋር ክልልን መሬት) ፋብሪካን ጨምሮ በድምሩ 12 አዳዲስ ስካY ፋብሪካዎችን የክልሎችን መሬት በፌዴራል መንግስት ስም በመንጠቅ በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ስካY ኮርፖሬሽን አጠቃላይ የግንባታ ስራ ወጭ 100 ቢሊዩን ብር (5.5 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር) እንደሚሆን ሲገመት ማሽነሪዎች ለመግዛት ግማሹ በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ይሻል፡የኢትዮጵያ ስካY ኮርፖሬሽን በአፋር ክልል ትንዳሆ 30 በመቶ ምርት በማምረት ላይ ሲገኝ በአሁኑ ግዜ በ394 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር ብድር ከህንድ አስመጭና ላኪ ባንክ(Export-Import Bank of India) በተገኘ ብድር የፋብሪካው ግንባታ ሥራ በህንድ(India's Overseas Infrastructure Alliance) በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡የኢትዮጵያ ስካY ኮርፖሬሽን በጥናት ላይ የተመሰረተ ሥራ እንደማይሰራ በምሁራኖች ዘንድ ይታወቃል፡፡የምስራቅና ምዕራብ አፍሪካ የንግድና ልማት ባንክ (ፒቲኤ ባንክ) ለኢትዮጵያ ስካY ኮርፖሬሽን 25 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር ብድር ለመስጠት ስምምነታ ላይ ተደርሶል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዲሴንበር 6/2011እኤአ  የቻይና አስመጭና ላኪ ባንክ( Chinese Export and Import Bank)ለኢትዮጵያ ዩኤስ 400 ሚሊዩን ዶለር (6.9 ቢሊዩን ብር) ሁለት  የብድር ስምምነቶች አድርገዋል፡፡ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር የባንኩ ምክትል ፕሬዜዳንት ዘሁ ሆንጃይ( Zhu Hongjie) እንደገለጹት ባንኩ 1.81ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር(31ቢሊዩን ብር) እንዳበደሩ ገልጸዋል፡፡አንዱ ስምምነት ባንኩ 100 ሚሊዩን ዶለር ለአዲስ አበባ የውሃ ሥራዎች አቅርቦት ፕሮጀክቶች ግንባታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር 300 ሚሊዩን ዶለር የባንኩን የብድር አቅርቦት ከፍ ለማድረግ እንደሆነ ተዘግቦል፡፡ ዘሁ ሆንጃይ እንደገለፁት ከሆነ ባንኩ እስካሁን 11.4 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር(272.2 ቢሊዩን ብር)እንዳበደሩ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮቴሌኮምበአጠቃላይ፣ከ2006 እኤአ እስከ 2013እኤአ የቻይና መንግስት ከቻይና የቴሌኮም ካንፓኒ፤ዜድቲኢ **ZTE Corporation**ና ሁዌ **Huawei Technologies Co. Ltd.** የቻይና ኮምኒስት ፓርቲ ንብረት የሆኑት ድርጅቶች ጋር የኢትዮጵያ ቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን (አሁን ኢትዮቴሌኮም) የ4.8 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር (72,142,100,000 ቢሊዩን ብር) ብድር በመፈራረም የእዳው ክፍያም ከኢትዩጵያ የሠሊጥ ምርት ወደ ቻይና በመላክ እንደሚወራረድ ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ በ1975 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 343.7 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 14% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ በ1991 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 9.1 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 214% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ በጁን 30 1999 ይሄ አሃዝ 10.2 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ከፍ ብሎል፡፡ በ2013 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 16.11ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር  የነበረ ሲሆን ይህውም ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 285.5% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ የውጭ ብድር ከፍተኛ እዳ ከተቆለለባቸው ደሃ አገራቶች መኃል የኢትዮጵያ አጠቃላይ የውጭ ብድር ከ20 እስከ 30 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር (373,036,000,000 ቢሊዩን ብር እስከ 559,554,000,000 ቢሊዩን ብር) እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ኢትዮ ቴሌኮምና የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለሥልጣን የመሳሰሉ ድርጅቶች በራሳቸው የሚያደርጉት የውጭ ብድር 11.5  ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ይገመታል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል 5 ቢሊዩን 490 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ብድር እንዳለበት ጥናቱ በዝርዝር ያሳያል፡፡ (ሀ) የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል1.2 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ከኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር **IFIs/Government to Sector Institutions on-lending** የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ሹማምንት ጋር ከተለያዩ ዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ተቆማቶች መኃል (*የዓለም ባንክ ዓለም ዓቀፍ ልማት ትብብር(* International Development Association (IDA)፣ የአፍሪካ የልማት ባንክ African Development Bank(AfDB)፣ የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ  European Investment Bank (EIB) etc.) ኮንሴሽናል ብድር (Concessionary loans) ለኤሌትሪክ አገልግሎት ዘርፉ አበድረዋል፡፡ኮንሴሽናል ብድር ዋንኛ ገፅታዎች አንደኛ ብድሩ የመካከለኛና የረጅም ግዜ ብድሮችን ሲያካትት፣ የብድሩ ግዜ ለሃያ ዓመታት መሆኑ፡፡ ሁለተኛ የብድሩ የእፎይታ ግዜ (grace period)  አምስት ዓመታት መሆኑና፡፡ በእፎይታ ግዜት ተበዳሪው መንግስት ወለዱን ብቻ እንጂ ዋናውን ገንዘብ (principal) መክፈል አይችልም፡፡ ሦስተኛ ተበዳሪዉ መንግስት የተበደረውን ገንዘብ በአነስተኛ ወለድ ከ3 እስከ 6 በመቶ ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይጠበቅበታል፡፡

**The Sector's Current Estimated Loan Portfolio የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል፣ኤሌትሪክ ኃይል ዘርፍ የውጭ ብድር**

| *Borrowing Source* የብድር ምንጭ | *Loan Amount US$ million* የዕዳ መጠን(ዩኤስ ዶለር በሚሊዩን) | *Repayment Period Years* የክፍያ ዘመን በአመት | *Grace Period years* የእፎይታ ግዜ | *Interest Rate %* የወለድ መጠን በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| IFIs/ Government on Lending | 1,250 | 20 | 5 | 5.00% |
| Commercial Banks | 1,000 | 10 | 3 | 6.00% |
| Bonds | 3,000 | 7 | 0 | 5.00% |
| Supplier's Credits | 240 | 4 | 1 | 5.00% |
| Total Current estimate | 5,490 | | (averages of categories used) | |

(ለ) የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል 1.0 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ከተለያዩ የንግድ ባንኮች ብድር ተበድሮል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የቻይናና የህንድ የንግድ ባንኮች ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የሀይድሮ ኤሌትሪክ ፓወር መሠረተ ልማት ዝርጋታና ግንባታ የሚውል ብድር ተበድረዋል፡፡ የንግድ ባንክ ብድር (Commercial Banks loans) ዋንኛ ገፅታዎች አንደኛ የብድሩ ግዜ ለአስር ዓመታት መሆኑ፡፡ ሁለተኛ የብድሩ የእፎይታ ግዜ ሦስት  ዓመታት ነው፡፡ በእፎይታ ግዜት ተበዳሪው መንግስት ወለዱን ብቻ እንጂ ዋናውን ገንዘብ መክፈል አይችልም፡፡ ሦስተኛ ተበዳሪዉ መንግስት የተበደረውን ገንዘብ በአነስተኛ ወለድ 6 በመቶ ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይጠበቅበታል፡፡

(ሐ) የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል 3 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር የቦንድ ብድር Bonds ከሃገር ውስጥና ከባህር ማዶ ዲያስፖራ፣ ከመንግስታዊና የግል ዘርፎች ቦንድ በመሸጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ የቦንድ ብድር (Bonds loans) ዋንኛ ገፅታዎች አንደኛ የብድሩ ግዜ ለሰባት ዓመታት መሆኑ፡፡ ሁለተኛ ተበዳሪዉ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል  የተበደረውን ገንዘብ በአነስተኛ ወለድ 5 በመቶ ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይጠበቅበታል፡፡ በኢትዮጵያ ባንኮች ከሚያበድሩት 27 በመቶ ለቦንድ ግዥ እንዲገዙ ግዳጁ እንደተጣለባቸው ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

(መ) የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል 240 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በዱቤ አቅራቢ ድርጅቶች **Supplier's credits** በብድር እቃዎች ተበድሮ ገዥቶል፡፡ የዱቤ አቅራቢ ድርጅቶች ብድር (**Supplier's credits**) ዋንኛ ገፅታዎች አንደኛ የብድሩ ግዜ ከ2 እስከ 4 ዓመታት መሆኑ፡፡ ሁለተኛ የብድሩ የእፎይታ ግዜ አንድ ዓመት ነው፡፡ ሦስተኛ ተበዳሪዉ መንግስት የተበደረውን ገንዘብ በአነስተኛ ወለድ ከ 4 እስከ 6 በመቶ ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይጠበቅበታል፡፡

የብድር አገልግሎት ***Debt Servicing:*** የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል የተበደረውን ገንዘብ ይሄ ሁሉ እዳ በአለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ በመሆኑ የእዳ ክፍያው ከላይ በተጠቀሰው የእፎይታ ግዜ ምክንያት ተበዳሪው ድርጅት ላይ ተፅዕኖ አያደርግም፡፡ ከዚህ በኃላ የብዙዎቹ እዳዎች የእፎይታ ግዜ ያልቅና የእዳው ክፍያ ከ 2012/13 እኤአ በኃላ ጀመ[ል፡፡ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይልና የመንግስት የብድር ጫና በተለይም የመንግስት የእዳ አገልግሎት ጫና 67 በመቶ በ2010 እኤአ እንደደረሰ ይታወቃል፡፡ በቀጣዩቹም አመታት ከ2013 እስከ 2018 እኤአ መከፈል ያለበት የእዳ አገልግሎት የክፍያ መጠን በአማካኝ 250 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ወይም (5 ቢሊዩን ብር)ና ከዛም በላይ ይሆናል፡፡ ይሄንንም ከሠንጠረዡ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

ለዚህም ዋና ማስረጃ የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት፣ ለኢትዮቴሌኮምና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል እዳ የኢትዮጵያ መንግስት እዳ እንዳልሆነና በብድሩም መንግስት ተጠያቂም እንዳአይደለ ለዓለምአቀፍ የገንዘብ ተቋም ማረጋገጡን በማስረጃ ቀርባል፡፡ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም (ኤይኤምኤፍ)ና የኢትዩጵያ መንግስት በጥቅምት 2014እኤአ የአንቀፅ አራት የምክክር አቅጣጫ (**IMF Country Report No. 14/303, THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA 2014 ARTICLE** Ⅳ **CONSULTATION**) ያወጣውን ሪፖርት ከድረ-ገፁ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

TOTAL PUBLIC DEBT OUTSTANDING Mn USD[1] (2009/10- 2013/14)

| | 2009/10 | | 2010/11 | | 2011/12 | | 2012/13[R] | | 2013/14[P] | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | USD | % | USD | % | USD | % | USD | % | USD | % |
| Total Public Debt | 11,496.68 | 100.00 | 14,633.69 | 100.00 | 17,600.64 | 100.00 | 22,085.42 | 100.00 | 25,703.25 | 100.00 |
| External Debt | 5,633.26 | 49.00 | 7,807.60 | 53.35 | 8,888.65 | 50.50 | 11,222.75 | 50.82 | 14,007.02 | 54.50 |
| Central Government | 3,695.61 | 32.14 | 4,724.98 | 32.29 | 5,469.28 | 31.07 | 6,831.51 | 30.93 | 8,419.24 | 32.76 |
| State Owned Enterprises | 1,937.65 | 16.85 | 3,082.62 | 21.07 | 3,419.37 | 19.43 | 4,391.24 | 19.88 | 5,587.78 | 21.74 |
| Domestic Debt | 5,863.42 | 51.00 | 6,826.09 | 46.65 | 8,711.99 | 49.50 | 10,862.67 | 49.18 | 11,696.23 | 45.50 |
| Central Government | 4,436.67 | 38.59 | 3,789.23 | 25.89 | 4,369.69 | 24.83 | 4,996.78 | 22.62 | 5,489.79 | 21.36 |
| State Owned Enterprises | 1,426.75 | 12.41 | 3,036.86 | 20.75 | 4,342.30 | 24.67 | 5.865.89 | 26.56 | 6,206.44 | 24.15 |

1.Domestic debt is changed into USD using Exchange Rate at end of period, R:Revised , P: Provisional ,Source:-Public Sector Debt Statistical Bulletin No 13 - Ministry of Finance ...www.mofed.gov.et/.../, Public%20Sector%20Debt%20Statistical%20Bulletin%20No%2013...

የኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ‹‹ የመንግስታዊ ዘርፍ የብድር መረጃ ስታስቲካል ቡሌቲን ቁጥር 13›› በሚል በድረ-ገጹ ላይ ካወጣው ሠንጠረዥን ፍሬ ሃሳብ ቀጥሎ በጥቂቱ ይገለፃል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከውጭ ብድር የተበደሩት (External Debt) በ2009/10 አምስት ነጥብ ስድስት(5.6) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣በ2010/11 ሰባት ነጥብ ስምንት (7.8) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2011/12 ስምንት ነጥብ ስምንት (8.8) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣በ2012/13 አስራ አንድ ነጥብ ሁለት (11.2) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2013/14 አስራ አራት (14.0) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ከውጭ ብድር እንዳለበት ጥናቱ ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከሃገር ውስጥ የተበደሩት( Domestic Debt) በ2009/10 አምስት ነጥብ ስመወንት (5.8) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣በ2010/11 ስድስት ነጥብ ስምንት (6.8) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2011/12 ስምንት ነጥብ ሰባት(8.7) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣በ2012/13 አስር ነጥብ ስምንት (10.8) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2013/14 አስራ አንድ ነጥብ ስድስት(11.6) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር የሃገር ውስጥ ብድር እንዳለበት ጥናቱ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከውጭ ብድርና( External Debt ) ከሃገር ውስጥ (Domestic Debt) የተበደሩት በ2009/10 አስራ አንድ ነጥብ አራት(11.4) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣በ2010/11 አስራ አራት ነጥብ ስድስት(14.6) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2011/12 አስራ ሰባት ነጥብ ስድስት(17.6) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣በ2012/13 ሃያ ሁለት(22.0) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2013/14 ሃያ አምስት ነጥብ ሰባት(25.7) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ከውጭና ከሃገር ውስጥ ብድር እንዳለባቸው ጥናቱ ያሳያል፡፡ በተረፈ ከድረ-ገፁ ላይ ጥናቱን ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

*Debt Policy:- "Since the debt relief granted under the Multilateral Debt Relief and Heavily Indebted Poor Countries initiatives (MDRI and HIPC) in 2006, Ethiopia's external debt stock has grown by more than four-fold, as a result of the surge in public enterprises' external borrowings from non-Paris-club and commercial banks. In 2012/13 the external debt stock rose to USD 11.1 billion from the previous year's level of USD 8.9 billion. The share of commercial banks in the outstanding external debt rose to 28% in 2012/13 from under 10% in 2007/08. On the other hand, the share of Paris-club donors shrank to 3.6% in 2012/13 from 4.6% in 2011/12. This may continue in light of the ambitious GTP investment agenda, which may pose risks to Ethiopia's debt rating and hence requires vigilance in debt management to mitigate the risk of debt distress. Any non-concessional borrowing should be consistent with maintaining a low risk of debt distress.The latest debt sustainability analyses*

*show that Ethiopia would remain at a low risk of external debt stress, despite the growth in external borrowing. Ethiopia will also remain at low risk of debt stress in 2013/14 and in 2014/15. The debt burden indicators are, however, on the rise." Source:- Ethiopia 2014, a.zerihun@afdb.org,haile.kibret@undp.org, james.wakiaga@undp.org,WWW.africaneconomicoutlook.org*

**ለዚህም ዋና ማስረጃ የህወሃት/ኢህአዲግ መንግስት ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅትና ለኢትዮቴሌኮም እዳ የኢትዮጵያ መንግስት እዳ እንዳልሆነና በብድሩም መንግስት ተጠያቂም እንዳአይደለ ለዓለምአቀፍ የገንዘብ ተቋም ማረጋገጡን በማስረጃ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም (ኤይኤምኤፍ)ና የኢትዩጵያ መንግስት በጥቅምት 2014እኤአ የአንቀፅ አራት የምክክር አቅጣጫ (ARTICLE IV CONSULTATION)ባወጣው ሪፖርት መሠረት:- ‹‹የኢትዩጵያ ባለስልጣናት አስተያየት የባለስልጣናቱ ከአጥኝው ባለሙያ ብድን ጋር በሃገሪቶ የውጭ እዳ ወይም ‹መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች› ብድር ላይ ስምምነት የላቸውም፡፡ ባለስልጣናቱ አስተያየት የኢትዩጵያ ቴሌኮም እዳ እንደ ኢትዩጵያ አየርመንገድ ብድር የኢትዩጵያ መንግስት ዋስትና አይሰጠውም፣ ስለዚህም እንደ ኢትዩጵያ መንግስት እዳ አይቆጠርም ወይም የመንግስት ብድር ሆኖ የመንግስት እዳ ላይ አይደመርም ይላሉ፡፡ ባለስልጣናቱ እንደሚያስረዱት እነዚህ ድርጅቶች እንደግል የንግድ ድርጅቶች ስራቸውን የሚያከናውኑ ናቸው፡፡የኢትዩጵያ አየርመንገድ ዓመታዊ የፋይናንስ ኦዲት ሪፖርት አውጥቶል እናም የኢትዩጵያ ቴሌኮም ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ነው፡፡›› ብለው ይከራከራሉ፡፡ በቻይና መንግስት ብድር የተነሳ ድርጅቶቹ፣ የቻይናኢትዬ አየርመንገድና ቻይናኢትዬ ቴሌኮም በአዋጅ እንደሚባሉ ወይም በእጅ አዙር እንደተሸጡ አመላካች ጥናት ነው፡፡የኢትዩጵያ መንግስት የአገሪቱን የውጭ እዳ በሚመለከት ከመንግስት ባለቤትነት የሚተዳደሩት ድርጅቶች የኢትዬጵያ አየር መንገድ፣ ኢትዬ ቴሌኮም፣ የኢትዬጵያ መብራት ኃይል ባለሥልጣን ከውጭ የሚበደሩት ብድርና የዕዳ መዝገብ ለብቻው ተነጥሎ እንዲታይ ይሞገታሉ፡፡ ኤይኤምኤፍ ደግሞ የሃገሪቱ ብድርና የዕዳ መዝገብ በአንድ ላይ መሆን እንዳለበት ማለትም ሃገሪቱ ከውጭ ንግድ ገቢዋ፣ከገቢ ንግድ ወጭዋ፣አጠቃላይ የንግድ ሚዛኖና የውጭ ዕዳዋ በአንድነት መሰላት አለበት ይላሉ፡፡ የእነዚህ መንግስታዊ ድርጅቶች ዕዳ በመንግስት የበጀት ድልድል ውስጥም የብድሩ መጠን፣የአከፋፈል ሁኔታና ውዝፍ እዳ ሁኔታ ሁሉ በአንድ ላይ መታየት እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ ኢትዩጵያ ያለባትን ጠቅላላ የዕዳ መጠን መንግስት በመደበቁ ምክንያትና ሀገሪቱ ዕዳውን ለመክፈል እማትችልበት ሁኔታ ላይ መድረሶንና የዕዳው ቁልል ወደአደገኛ ደረጃ እየደረሰ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የጥናቱን ዝርዝር ከድረ-ገፁ ያንብቡት፡፡ *Authorities' views:-* Authorities do not concur with the staff's assessment of the public debt**. They maintain that Ethiopian-Telecom liabilities, like those of Ethiopian Airlines, are not guaranteed by the government and hence should not be added to government debt. They explain that both these entities operate as commercial enterprises. Ethiopian Airlines discloses audited annual financial statements and Ethiopian-Telecom is in the process of doing so.

**በመቀጠልም ጥናቱ ስለ ማህበረሰብ ዘርፍ እዳ ያትታል፤መነበብ ያለበት ዶሴ ነው፡፡ የሃገሪቱን አጠቃላይ ኢኮኖሚ ግብርና፣ ኢንደስትሪና አገልግሎት ዘርፎች በመረጃና ጥናት ላይ ተመስርቶ በማቅረብ መጭውን ትውልድ ስለ ሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በማሳወቅ ወጣት የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎችን ማፍራት የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ የሃገሪቱን ፖለቲካ በትረ ሥልጣን ለመጨበጥ ኢኮኖሚውን ማወቅ ግድ ይላል፡፡**

## ሉዓላዊ የቃል ኪዳን ሰነድና የኢትዩጵያ ኢኮኖሚ ተጨባጭ ሁኔታ ስኬቶችና ድክመቶች

*1-የባህር ማዶ ልማት ትብብር (ODA፡ Official Development Assistance) ከ1991እኤአ እስከ 2012 እኤአ ለህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት አርባ ቢሊዮን ዶላር የልማት እርዳታ ሰጥተዋል፡፡ በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በአማካኝ በአመት ሁለት ቢሊዮን ዶላር እርዳታ ሃገሪቱ እንዳገኘች ያስረዳል፡፡ በይፋ የተለያዩ ለጋሽ ሃገራት የሰጡትን ገንዘብ ብዛትን ለማስላት ያህል በትንሹ ስምንት ታላቁን የህዳሴ ግድብ ኤሌትሪክ ማመንጫን በእርዳታ ገንዘቡ ለመስራት የሚያስችል ሜጋ ፕሮጀክት ነበር፡፡ወይም የቻይና መንግስት በ200 ሚሊዮን ዶለር ያሰራውን የአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ህንፃን ዓይነት ሁለት መቶ ህንፃዎች ሊገነባ የሚችል ገንዘብ ነበር፡፡አጠቃላይ ዝርዝሩን ከሰንጠረዡ ላይ ያስተውሉ፡፡*

*ከምዕራባዊያን አገራት የልማት እርዳታ ኢትዬጵያ ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ 40 ቢሊዮን ዶለር ያገኘች የአፍሪካ ብቸኛ ሃገር ናት፡፡ የልማት ዕርዳታ ካደረጉት ሃገራት መኃል፤ ከአሜሪካ፣ከእንግሊዝ፣ ከጀርመን ፣ከካናዳ፣ከጣልያን፣ከኒዘርላንድ፣ከጃፓን መንግስታት ግብር ከፋይ ህዝብ ለኢትዬጵያ መንግስት ገፁበረከት የቀረበ ሲሆን ገንዘቡ ለምን ዓይነት ልማት እንደዋለ የተሰጠ አንዳችም ማረጋገጭና ማስረጃ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከ1991 እስከ 2010 እኤአ በህወሃግ/ኢህአዲግ ዘመነ አገዛዝ፤ በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 15,903.2 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር ከኢትዬጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተመልሶ ተቀምጦል፡፡ ለዚህ ነው ግብር ከፋዩ የባህር ማዶ ህዝብ ገንዘብ ለሌቦችና ለዘራፊዎች እንደዋለ ዓለም ዓቀፍ ጥናቱ በማሰረጃ ያረጋገጠው፡፡*

| *Year* | *1991* | *1992* | *1993* | *1994* | *1995* | *1996* | *1997* | *1998* | *1999* | *2000* | *Total 1991-1999* |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *Capital Flight* | *538* | *-590.5* | *-327.9* | *226.0* | *139.5* | *26.8* | *614.9* | *456.5* | *-675.6* | *406.2* | *813.9* |

| *Year* | *2001* | *2002* | *2003* | *2004* | *2005* | *2006* | *2007* | *2008* | *2009* | *2010* | *Total 1991-2010* | *Grand Total 1970-2010* |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *Capital Flight* | *2518.0* | *3073.4* | *1598.4* | *1400.8* | *-319.9* | *104.0* | *1695.6* | *-263.8* | *1875.1* | *3407.7* | *15,089.3* | *24,874.8* |

*Source: Source: Authors' computation.(Capital Flight from Sub-Saharan African Countries: Updated Estimates,1970-2010)*

*በአጠቃላይ ከ1991 እስከ 2010 እኤአ በህወሃግ/ኢህአዲግ ዘመነ አገዛዝ፤ በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 15,903.2 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር ከኢትዬጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተቀምጦል፡፡ በ2014እኤአ የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር 300 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ እንዲሁም የአሜሪካ ዓለም ዓቀፍ ልማት 600 ሚሊዮን ዶለር ለኢትዬጵያ መንግስት በእርዳታ ለመስጠት ስምምነት ፈፅመዋል፡፡*

*የዓለም ዓቀፍ ተዋህዶ ፋይናንስ* 'Global Financial Integrity (GFI) *ምርምርና ጥናት የመጀመሪያ ትኩረት ህገወጥ የፋይናንስ /የገንዘብ ዝውውርና ፍሰት እናየውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኩብለላን መግታትና ማገድ ነው፡፡ የዓለም ዓቀፍ ተዋህዶ ፋይናንስ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርና ፍሰት ድህነትን ያለና የሚኖር ዘላለማዊ ያደርገዋል ይላል፡፡ ደሃ አገራት አንድ ዶለር ከባህርማዶ እርዳታ በተቀበሉ ግዜ፤ከአገራቸው በህገወጥ መንገድ አስር ዶለር ወደ ውጭ ሃገር ይወጣል፡፡ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርና ፍሰት አሊያም ቁሻሻ ገንዘብ መግታት ካልተቻለ፤በዓለማችን ሱስ የሚያሲዝ ዕፅ አሰራጭ ኩባንያዎች ይስፋፋሉ፣ ሽብርተኛ ድርጅቶች ይፈለፈላሉ፣እናም ግብር የማይከፍሉ ካንፓኒዎችና ድርጅቶች በህቡዕ /በሚስጢር ገንዘብ በአለም ላይ ያዘዋውራሉ፡፡ በሦስተኛው አለም ሃገራት በተዘረፈ ብዙ ቢሊዮን ዶላሮች የተነሳ የታዳጊ ሃገሮችን የተፈጥሮና የሰው ልማት ሃብት ድህነት በመመንመን ሃገራቱ*

*ከወደቁ መንግስታት ተራና ጎራ እንዲፈረጁ ይዳረጋሉ። የባህር ማዶ ልማት ትብብር የልማት እርዳታ ቀጣይነት አጠያያቂ ይመስላል ሕወሃት/ኢህአዴግ መንግስት የእዝ ኢኮኖሚና የአንድ አውራ ፖለቲካ በትረ-ስልጣን የአውሮፓና የአሜሪካ መንግስታትን የእርዳታ ድጋፍ ዘላቂነት አጠያያቂ ያደርገዋል።*

## *2-በኢትዮጵያ ከውጭ የተላከ ገንዘብ/ የውጭ ሐዋላ*

*በ1995 እኤአ ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ 27 ሚሊዮን ዶለር፣በ2000 እኤአ 53 ሚሊዮን ዶለር መድረሱን የብሄራዊ ባንክ ገዥ ይፋ አድርጓል። በግምት አንድ ሚሊዮን ከሚሆኑት ባህር ማዶ ሃገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሰደተኛች በ2012 እኤአ ከ1.2 እስከ 2.4 ቢሊዮን ዶለር ከውጭ ሐዋላ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገባ የብሄራዊ ባንክ ገልፆል። በዚህም መሠረት ከባህር ማዶ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሃገር ውስጥ የተላከ ገንዘብ የዓለም ባንክ ባወጣው መረጃ፣ ከሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው ዝቅተኛ ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ በ2001 እኤአ 18 ሚሊዮን ዶለር የነበረ ሲሆን ከፍተኛ 3 ቢሊዮን ዩኤስ ዶላር በ2013እኤአ እድረት እንዳሳየ መረዳት ይቻላል። በ2014 እኤአ የዘጠኝ ወራት ሪፖርት መሠረት ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ ሁለት ቢሊዮን ዶለር ገደማ መድረሱን የብሄራዊ ባንክ ገዥ ይፋ አድርጓል። በዚህም መሠረት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገናቸውን በመርዳትና በማስተዳደር የሲሶ መንግስትነት ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛሉ ሰለዚህም በሀገራቸው ጉዳይ ከማንም በላይ ሊያገባቸውና ድምፃቸውም ሊሰማ ይገባቸዋል።*

Inward Remittances, Ethiopia 2000-2014

| Year | 2000 | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Remittances (USD Million) | 53 | 18 | 33 | 46 | 134 | 174 | 172 | 358 | 387 | 262 | 345 | 371 | 2.4 Billion | 3 Billion | 2 Billion |
| % | | -34 | 183 | 139 | 291 | 130 | 99 | 208 | 108 | 68 | 132 | 107 | 647 | 125 | -67 |

Sources: Extracted from: The World Bank (2012) Remittances Data-inflow.

*የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኩብለላ ከሃገረ ኢትዮጵያ ወደ ባህር ማዶ ሃገራት (Illegal Ethiopian Capital Flight) በሚለው ጥናታዊ ፅሑፍ እንደተገለፀው ከሆነ፣6-Unrecorded remittances (ያልተመዘገቡ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ነዋሪዎች የተላከ የውጭ ሐዋላ 6.0 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር እንደነበረ ተዘግቦል። በአጠቃላይ ከ1970 እስከ 2010 እኤአ በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 24,874.8 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር ከኢትዮጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተቀምጦል።ከ1970 እስከ 2010 እኤአ ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ ሸቀጦች በዝቅተኛ ዋጋ ደረሰኝ የተገዙ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ በቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር 1) አጠቃላይ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታል(Total capital flight) 24.9 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር)፣2) ያልተስተካከል‹ቀሪ›ሂሳብ(Unadjusted 'residual' measure ) 25.9 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር)፣3) ወደ ውጭ ከተላኩ ሸቀጦች በዝቅተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተሸጡ( Export misinvoicing ) 2.5 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር)፣4) ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ ሸቀጦች በከፍተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተገዙ( Import misinvoicing ) -9.5 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር)፣5) አጠቃላይ ንግድ በዝቅተኛና በከፍተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተሸጡና የተገዙ(Total trade misinvoicing ) -7.1 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር)፣6) ያልተመዘገቡ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ሃገር ቤት ላሉ ቤተሰቦችና ዘመዶች የተላኩ የገንዘብ ድጎማዎች (Unrecorded remittances) 6.0 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር)የዓለም ባንክና የዓለም ዓቀፍ ገንዘብ ድርጅት መረጃ ጥናት መሠረት በተለይም የውጭ ሐዋላ ፍሰት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከሃገር የሚወጣና የሚገባ ገንዘብ ልዩነት እንዳለው በመረጃ ተደግፎ ተገልፆል። በዚህም ምክንያት በዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ሐዋላ ፍሰት በሚመለከት ተመዝግቦ የሚቀረበው ሪፖርት የተዛባ መሆኑ በጥናት ይታወቃል። በኢትጵያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ሐዋላ ፍሰት ከመደበኛ(ህጋዊ) በሆነ መንገድና(መኒ ግርሃም፣ ዌስተርን ዩኒየን፣ድሃብሽን ወዘተ) እንዲሁም በአመዛኙ መደበኛ ባልሆነ (ህገወጥ) መንገድ እንደሚሰበሰብ ይታመናል።ከ1970 እስከ 2010 እኤአ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ሃገር ቤት ላሉ ቤተሰቦችና ዘመዶች የተላከ ገንዘብ ወይም ያልተመዘገቡ የውጭ ሐዋላ (Unrecorded remittances) 6.0 ቢሊዮን ዩኤስኤ ዶለር ሲሆን፤ በአርባው አመታት ውስጥ በአማካኝ 150,000,000 ሚሊዮን ዩኤስኤ ዶለር በየዓመቱ በህገወጥ መንገድ ተዘርፎል ማለት ይቻላል።ኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በ2010 እኤአ ብቻ መደበኛ ባልሆነ መንገድ 428 ሚሊዮን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ በግለሰቦች የተዘረፈ የውጭ ሐዋላ ንዋየ-ቅሸባ መፈፀሙን በግልፅ ተገልፆል። The NBE QuarterlyBulletin reports that of the above individual transfers, $428 million was "underground private transfers" (NBE 2010). ተብሎ ተገልፆል። ይሄን የሚያህል የድሃ አገር ህዝብ ገንዘብ ሲዘረፍ፣ዘራፊው እራሱ በሙስና የተጨማለቀ መንግስት እንደሆነ እማኝ ማቅረብ ካስፈለገ አባቱ ዳኛ፣ ልጁ ቀማኛ ተብሎልና አንድ በሉ።*

*በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመነ አገዛዝ፣ በውጭ ሃገራት ልጆቻቸውን ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምሩ የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣኖች፣ ነጋዴዎች፣ ወዘተ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በሚሊዮን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ በግለሰቦች የተዘረፈ የውጭ ሐዋላ ንዋየ-ቅሸባ በማድረግ ለልጆቻቸው የትምህርት ቤት ክፍያ ይፈፀማሉ። ይሄንን መረጃ ለማግኘት የነማን ልጆች ውጭ ይማራሉ፤ብዛታቸው ስንት ነው፣ የዩኒቨርሲቲው ክፍያ በአመት ስንት ዶለር ነው፣ወዘተ የመረጃ መጠይቆችን ግዜ ያወጣዋል።ዛሬ በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመነ አገዛዝ የደሃ ልጆች ከባህር ማዶ ሃገራት በመቶ ሽህ ዩኤስ ዶላር በመናጢ ደሃ አባቶቻቸው እየተከፈለላቸው ይማራሉ። እነዚህ የመንፈስና የህሊና ደሃ ሃገር መሪዎች ምርጥ አስተማሪ በጥሩ ክፍያ ሃገር ውስጥ አምጥቶ ማስተማር እየተቻለ የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሪና ሃብት በዚህ መልክ ይዘርፋሉ።ሌላው በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን የስርአቱ ሹመኞች በውጭ ሃገራት ህክምና በማድረግ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በቡዙ ሚሊዮን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ የተዘረፈ የውጭ ሐዋላ ንዋየ-ቅሸባ በማድረግ የኢፈርትና የሜድሮክ ባንኮችና ኩባንያዎች ስውር የውጭ ሃገር የባንክ አካውንት በመክፈት ሹመኞች በታመሙ ግዜ ከነጠባቂ ወርዲያዋቻቸው ወደ ባህር ማዶ ሆስፒታሎች በመሄድ ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ።*

*ለማጠቃለያ በተባበሩት መንግስታት የሠላም አስከባሪ በመሆን ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ሠራዊት የደሃው የገበሬ ልጆች ያፈራቸው፤ በውጭ ምንዛሪ የሚገኙትን የወር ደሞዝ ክፍያ፤ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በሚሊዮን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ በህወሃት/ኢህአዴግ ሹማምንት፤ የጦር አበጋዞች ‹ጀነራል መኮንኖች› እየተዘረፈ ለሠራዊቱ አባሎች በብር በመክፈል ዶለሩን ይዘርፋሉ በሠራዊቱ ደም ይነግዳሉ። ሹማምንቱ ባግበሰበሱት የውጭ ሐዋላ የዶላር ንዋየ-ቅሸባ፣ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ይገነባሉ።የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ይሄ ሁሉ መረጃ እንዳለውና ወደፊት ግዜ የሰጠውና ሃገሬ ያለ ዜጋ እንደሚያጋልጠው ሳይታለም የተፈታ ነው። ከባህር ማዶ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የታላቁ ህዳሴ የቦንድ ሽያጭ በማምከን ድጋፋቸውን ነስተዋል። ኢትዮጵያውያኑ ሃገራቸውን በእውቀትና በገንዘብ እንዲያግዙ የስብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መብትን ማክበር፣ ነፃ ምርጫ፣ነፃ ኢኮኖሚ የመሳሰሉትን ህዝባዊ ጥያቂዎች፣ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት ያሞላል ብሎ መጠበቅ የህልም እንጀራ በመሆኑ ውጭ የሚኖሩ ዜጎችን ድጋፍ ማግኘት አይቻለውም።*

## *3-የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ Chinese Foreign Direct Investment (FDI)* in Ethiopia

የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በአፍሪካ በአለፈው አስር ዓመታት በምሁራኖች፣በፖሊሲ አውጭዎችና በብዙሃን መገናኛ ትልቅ ትኩረት ስቦል። የቻይና ኢንቨስትመንት በአፍሪካ በአመዛኙ በነዳጅ፣በሚኒራልና በተፈጥሮ ጥሬ ሃብቶች ለምሳሌ ስኮርና ጎማ ምርቶች ላይ ያተኩራል። የቻይና ኢንቨስትመንት በመሰረተልማት ዘርፍ ላይ በቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ፣ በመንገድና ባቡር ትራንስፖርት ዘርፎች እንዲሁም በስታዲምና መንግስት ቢሮዎች ግንባታ ላይ ያተኩራል። የቻይና ኢንቨስትመንት በማንዩፋክቸሪንግ ዘርፍ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ ተሰማርተው ይገኛሉ። የቻይና ኢንቨስትመንት በአፍሪካ ልዩ ኢንደስትሪያል ዞኖች በማቆቆም የኢኮኖሚውን ዘርፍ በመደገፍ ላይ ይገኛሉ።በአጠቃላይ ሰባት የአፍሪካ አገራቶች መኃል አንጎላ፣ደቡብ አፍሪካ፣ሱዳን፣ኮንጎ፣ጊኒ፣ናይጀሪያና ጋቦን 90 በመቶ የተፈጥሮ ጥሬ እቃዎች ወደ ቻይና ይልካሉ።

እንደ ሽይእር( Schiere (2011) የቻይና ንግድና የኢንቨስትመንት ፍሰት ሁሉንም የአፍሪካ አገራት ኢኮኖሚ ዘርፎች በእኩልነት አልጠቀመም የአፍሪካ ሃገራት ወደ ቻይና የሚልኩት ሸቀጣ ሸቀጥ 70% በመቶ ከአንጎላ(የነዳጅ ምርት)፣ደቡብ አፍሪካ(ብረት፣አልማዝ፣ፕላቲነም፣ማንጋኒዝ፣

መዳብና አልሙኒየም )፣ ሱዳን(የነዳጅ ምርት)ና ከዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ኮንጎ(የተለያዩ ጥሬ እቃዎች) በአመዛኙ በተፈጥሮ ሃብቶችን ያስገባሉ፡፡ ከቻይና ወደ አፍሪካ አገሮች 60 በመቶ ከሚገቡት የማንፋክቸር እቃዎች ወደ ግብፅ፣ ናይጀሪያ፣አልጀሪያና ሞሮኮ ሃገራት ነው፡፡

የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በአፍሪካ አገራት በከፍተኛ መጠን በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ ከቻይና ወደ አፍሪካ ጠቅላላ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ከ2004 እኤአ 5,497,990,000 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር፣ በ2010 እኤአ 68,811,310,000 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር ከፍ እንዳለ ከሠንጠረዡ ማስተዋል ይቻላል፡፡

ዓመታዊ የቻይና ጠቅላላ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ከ2004 እስከ 2010 እኤአ በአፍሪካ፣ በደቡብ አፍሪካ፣በናይጀሪያ፣ በሱዳን፣ በአልጀሪያ፣ እንዲሁም በኢትዩጵያ፣ የቻይና ጠቅላላ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ዝቅተኛው 0.43(0.0078%)፣ከፍተኛው 74.29(0.1314%) ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር እድገት አሳይቶል፡፡ ከ2004እኤአ እስከ 2010 እኤአ አጠቃላይ ዓመታዊ የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በአፍሪካ ያደረገችው ከኢትዩጵያ ጋር ሲነፃፀር ከአንድ በመቶ ያነሰ መሆኑን ሠንጠረዡ ያሳያል፡፡

China's outward FDI flows by country, 2004-2010 (millions of US$)

Direct Investment from China to Ethiopia, 2004 to 2010: Annual Chinese FDI into Ethiopia (US$ million)

| ተ.ቁ No | ዓመት year | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በአፍሪካ ጠቅላላ FDI | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በደቡብ አፍሪካ FDI | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በናይጀሪያ FDI | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በሱዳን FDI | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በአልጀሪያ FDI | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በኢትዩጵያ FDI | የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በአፍሪካ ጠቅላላ ከኢትዩጵያ በመቶ(%) FDI |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2004 | 5497.99 | 17.81 | 45.52 | 146.70 | 11.21 | 0.43 | 0.0078 |
| 2 | 2005 | 12261.17 | 47.47 | 53.30 | 91.13 | 84.87 | 4.93 | 0.0402 |
| 3 | 2006 | 17633.97 | 40.74 | 67.79 | 50.79 | 98.93 | 23.95 | 0.1358 |
| 4 | 2007 | 26506.09 | 454.41 | 390.35 | 65.40 | 145.92 | 13.28 | 0.0501 |
| 5 | 2008 | 55907.17 | 4807.86 | 162.56 | 63.14 | 42.25 | 9.71 | 0.0173 |
| 6 | 2009 | 56528.99 | 41.59 | 171.86 | 19.30 | 228.76 | 74.29 | 0.1314 |
| 7 | 2010 | 68811.31 | 411.17 | 184.89 | 30.96 | 186.00 | 58.53 | 0.0850 |

*Source:* 2010 Statistical Bulletin of China's Outward Foreign Direct Investment, FDI Bulletin of the Chinese Ministry of Commerce: ODI Statistics (2010).

እንደ ብራውቲጋም (Brautigam, 2009) የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በአፍሪካ አገራት በከፍተኛ መጠን በመጨመር ላይ ቢገኝም ቅሉ 50 በመቶ የሚሆነው ኢንቨስትመንት በማዕድን ዘርፍ ሃብታም የሆኑ አገራት ናይጀሪያ፣ ደቡብ አፍሪካና ሱዳን በመሳሰሉት ላይ የተደረጉ ናቸው፡፡ የቻይና መንግስት ፖሊሲ መሠረት በባህር ማዶ አገራት የግብርና ዘርፎን ኢንቨስትመንት ማስፋፋትነው፡፡ ሆኖም የግብርና ዘርፎን ኢንቨስትመንት ከማዕድን ዘርፍና ማንፋክቸሪግ ዘርፎች አንፃር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጦል፡፡

''Chinese outward FDI to Africa shows a similar pattern of concentration, with 50% flowing to the mining sectors of just a handful of resource-rich countries (Nigeria, South Africa and Sudan). The Chinese government *going global* policies encourages overseas agricultural investment. However, outward investment in agriculture and related activities is much smaller than in mining or manufacturing (Brautigam, 2009).''

<u>**የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በኢትዩጵያ ውስጥ በመቶኛ ሲነፃፀር**</u>

የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በአፍሪካ አገራት በከፍተኛ መጠን በመጨመር ላይ ሲሆን በተለይ በኢትዩጵያ ልዩ አትኩሮት በቻይና በኩል ተሰጥቶታል፡፡ በኢትዩጵያ የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን መሳብ የቻለው በሃገሪቱ ውስጥ ባለው ርካሽ የሠራተኛ ጉልበት ዋጋ፣ በአነስተኛ የመሬት ዋጋ ሽያጭ፣በሃገሪቱ ውስጥ ባለው ገበያ እንዲሁም መንግስት ባደረገው ማበረታቻ ለምሳሌ የታክስ እፎይታና ከውጭ ለሚገቡ እቃዎች/ማሽነሪዎች ወዘተ ከቀረጥ ነፃ የማስገባት መመሪያና ፖሊሲ በማውጣት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ችሎል፡፡ በሌላ በኩልም በምስራቅ ኤሲያ ሃገራት የሰራተኛ ጉልበት ክፍያ ማሻቀብ፣ የመሬት ሽያጭ ዋጋ መጨመርና የተወዳዳሪ ካንፓኒዎች ፉክክር በማየሉ የተነሳ አፍሪካ የመሳሰሉ ክፍለ ዓለማት ትኩረት እንዲያገኙ ሲረዳ በተለይም በአፍሪካ ላይ የፖለቲካ መስፋፋት ለማድረግ ባለው ፉክክር ቻይና በለስ የቀናት ሃገር ለመሆን በቅታለች፡፡

የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በኢትዩጵያ 0.4 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በ2004 እኤአ የነበረ ሲሆን፤ 4.9 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በ2005፤ 24.0 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በ2005 እየጨመረ በመሄድ በ2009 እኤአ 74.3 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር እንደደረሰ ከሠንጠረዡ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡ እንደ ኢትዩጵያ ኢንደስትሪ ሚኒስትር መረጃ መሠረት 372 የቻይና ኢንቨስተሮች በ2012 እኤአ በይፋና በግልፅ እንደተመዘገቡ ታውቆል፡፡ ይህ አሃዝ በአገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የቻይና ኢንቨስተሮች አይጨምርም፡፡

በቻይናና ኢትዩጵያ መኃል የንግድ እንቅስቃሴ ፍሰት ፤የእርዳታ ፍሰት ፣የአስተዳደር ልምድና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ዋናዎቹ የኢኮኖሚ ግንኙነት ስምምነቶች ናቸው፡፡ ከአራቱ ማኃል የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በረዥም ግዜ ውስጥ በሃገሪቱ ኢኮኖሚው ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ነፃ ገበያ እንዲያድግ፣የቴክኖሎጅ ልውውጥ እንዲዳብርና በዓለም ዓቀፍ የምርት ትስስርና ልውውጥ እንዲበለፅግ ሃይል ይሰጠዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በ2012 የዓለም ባንክ ጠቅላላ ምርምርና የአሰሳ ጥናት መሠረት፤ የቻይና ካንፓኒዎች የባለቤትነት ድርሻ የቻይና የግሉ ዘርፍ 69 በመቶ፤ የቻይናና የኢትዩጵያ ኃ/የ/የግል ማህበራት 15 በመቶ፤የቻይና መንግስታዊ ዘርፍ 13 በመቶ እንዲሁም የተለያዩ 3 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡According to the Ethiopian Herald 15, July 2014 entitled ''US, European investment flow growing"

"Over the past 10 years, the FDI flow most of the investment comes from Asian countries especially China and India. But now investment flows at nearly equal rate from Europe, amerrica and Asia. Of the total 40.61 billion Birr (app. US$ 2 Billion) Foreign Direct Investment (FDI) between mid 2010 and mid 2014 the share of US and European investment is over 19.27 billion Birr, about 47 per cent, according to data. "

የቻይና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በኢትዩጵያ እየተሞጠጠ የመጣ ይመስላል፣ ባደረጉት ልዩ ልዩ ኢንቨስትመንትና ኢንደስትሪያል ዞኖች ያገኙት ገቢ ከጠበቁት በታች ሆኖል፡፡ ሃገሪቱ የባህር በር ስለሌላት ለተጨማሪ ወጭዎች ተዳርገዋል፣ቢሮክራሲው ችግር፣የቀረጥና የታክስ ከፍተኛ መሆን፣የሰለጠነ ሰው ችግር፣ሙስናና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ወዘተ ችግሮች ተስፋ አስቆርጦቸዋል፡፡ በቻይና 400 ሚሊዩን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ማለትም ከአንድ እስከ ሁለት ዶላር የቀን ገቢ ያላቸው ድሃ ህዝቦች ያላት ሃገር መሆኖን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

**4-የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኩብለላ ከሃገረ ኢትዩጵያ ወደ ባህር ማዶ ሃገራትIllegal Ethiopian Capital Flight**

በአለፉት 40 አመታት ውስጥ፣ከኢትዩጵያ የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኩብለላ በብዙ ቢሊዩን ዶላር በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሃገራቶች እንደወጣ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ ኢትዩጵያ ከአለማችን ከሚገኙ ደሃ አገራቶች ውስጥ ከመጨረሻዎቹ ጠርዝ ላይ የምትገኝ ስትሆን ይሄን የሚያህል የውጭ ምንዛሪ ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ ሲኮበልል የሃገሪቶን እድገት በማቀጨጭ ስርዐቱ ምን ያህል በሙስና የተጨማለቀ፣ግልፅነት የጎደለው መንግስታዊ አደረጃጀትና አሰራር በሃገሪቱ እንደሰፈነ ያሳያል እንዲሁም ተጠያቂነት የሌለበት የሽፍቶች፤ የነዱር ቤቴ ዘመን በከተሞች የሰፈነ ይመስላል፡፡ ሰባ ከመቶ የሚሆነው የኢትዩጵያ ህዝቡ በቀን ከአንድና ሁለት ዶለር ገቢ እያገኘ በሚኖርባት የድሆች፣ የርሃብተኞች፣ የበሽተኞች ሃገር ይሄን የሚያህል የገንዘብ ነጠቃ ምን ይባላል፡፡ ጅቦች የሚያስተዳድሮት ሃገር ከማለት በስተቀር፡፡በኦክቶበር 2012 እኤአ ፕሮፌሰር ሊዎንስ ኤንዲኩማንና ፕሮፌሰር ጅምስ ኬ ቦይስ በማሳቹሴት ዩኒቨርሲቲ አመህርስት፤ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ጥናትና ምርምር

ኢንስቲትውት፤ ባቀረቡት የጥናት ርዕስ ‹የንዋይ ኩብለላ በስብ ሳህራ አፍሪካ አገሮች ከ1970 እስከ 2010›[1] ጥናታዊ ሪፖርት መሠረት ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገሮች የኮበለለ የውጭ ምንዛሪ ከ1970 እስከ 2010 ድረስ ምን ያህል በየአመቱ እንደአደገና በየአስር አመቱም እምርታውን እየጨመረ መሄዱን ከጥናቱ ለመቃኘት ይቻላል፡፡""***Capital Flight:*** *A destructive process in which investors (both foreigners and domestic residents) withdraw their financial capital from a country as a result of what are perceived to be non-favourable changes in economic policies, political conditions, or other factors. The consequences of capital flight can include a contraction in real investment spending, a dramatic depreciation in the exchange rate, and a rapid tightening of credit conditions. Developing countries are most vulnerable to capital flight."*

በህወሃግ/ኢህአዲግ ዘመነ አገዛዝ ከ1991 እሰከ 2010 እኤአ የንዋይ ኩብለላ 15,903.2 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ አገራት ተመንትፎል፡፡

| Year | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 | 1998 | 1999 | 2000 | Total 1991-1999 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Capital Flight | 538 | -590.5 | -327.9 | 226.0 | 139.5 | 26.8 | 614.9 | 456.5 | -675.6 | 406.2 | 813.9 |

| Year | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | Total 2001-2010 | Grand Total 1970-2010 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Capital Flight | 2518.0 | 3073.4 | 1598.4 | 1400.8 | -319.9 | 104.0 | 1695.6 | -263.8 | 1875.1 | 3407.7 | 15,089.3 | 24,874.8 |

Source: *Source: Authors' computation.(*Capital Flight from Sub-Saharan African Countries: Updated Estimates,1970-2010)

በአጠቃላይ ከ1991 እሰከ 2010 እኤአ በህወሃግ/ኢህአዲግ ዘመነ አገዛዝ፤ በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 15,903.2 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ከኢትዮጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተቀምጦል፡፡በአጠቃላይ ከ1970 እሰከ 2010 እኤአ በሦስቱ አገዛዝ ዘመን፤(በወታደራዊው ደርግና በህወሃግ/ኢህአዲግ) በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 24,874.8 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ከኢትዮጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተቀምጦል፡፡

ADJUSTMENT FOR TRADE MISINVOICING AND UNRECORDED REMITTANCES,1970-2010 (BILLION, CONSTANT 2010 $)

| Country Name | Total capital flight | Unadjusted 'residual' measure | Export misinvoicing | Import misinvoicing | Total trade misinvoicing | Unrecorded remittances |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Ethiopia | 24.9 | 25.9 | 2.5 | -9.5 | -7.1 | 6.0 |

Source: - CAPITAL F L I GHT FROM SUB-SAHARAN AFRICAN COUNTRIES PAGE 18

*Capital Flight from Sub-Saharan African Countries: Updated Estimates,1970– 2010,* **James K. Boyce and Léonce Ndikumana**

Political Economy Research Institute University of Massachusetts, Amherst October 2012,Read more at the PERI website.

ከ1970 እስከ 2010 እኤአ ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ ሸቀጦች በዝቅተኛ ዋጋ ደረሰኝ የተገዙ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ በቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር

1-Total capital flight (አጠቃላይ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታል 24.9 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

2-Unadjusted 'residual' measure (ያልተስተካከል‹ቀሪ›ሂሳብ 25.9 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

3-Export misinvoicing (ወደ ውጭ ከተላኩ ሸቀጦች በዝቅተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተሸጡ 2.5 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

4-Import misinvoicing (ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ ሸቀጦች በከፍተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተገዙ -9.5 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

5-Total trade misinvoicing ((አጠቃላይ ንግድ በዝቅተኛና በከፍተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተሸጡና የተገዙ -7.1 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

6-Unrecorded remittances (ያልተመዘገቡ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ሃገር ቤት ላሉ ቤተሰቦችና ዘመዶች የተላኩ የገንዘብ ድጎማዎች 6.0 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

የሃገር ቤት የሃብት ክምችት ዋና ምንጭ ብሄራዊ የቁጠባ ተቀማጭ ገንዘብ( domestic saving) ሲሆን ይህ ባህልን በማዳበርና መልሶ ኢንቨስት በማድረግ ብዙ ሰዎችን በፋብሪካዎች ውስጥ ቀጥሮ በማሰራት፣ እራስንና ሃገርን በመጥቀም ዜጎችንና ሃገርን የማዝመን ስራ መከወን ነው፡፡ በዚህም የተቀደሰ ሥራ ህዝቡ ከረሃብ ፣ከድህነትና ከበሽታ ተጠብቆ አምራች ሃይል እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በሰራተኛው ህዝብ ተመርቶ ወደ ውጭ ሃገራት የተላከው ምርት የውጭ ምንዛሪ አስገኝተው ከባህር ማዶ ሃገራት፣ ሃገራችን የምትፈልገውን ማሽነሪዎች፣ ካፒታል ጉድስ፣ መድሃኒቶች፣ማዳበሪያዎች ወዘተ በማስገባት ልማት ማፋጠን ይቻላታል፡፡ የኢኮኖሚ እድገት መሰረቱ ኢንቨስትመንት ነው፣ የተትረፈረፈ ምርት ያስገኛል ይህንንም ሸጦና ለውጦ በትርፉ ድጋሚ ኢንቨስት በማድረግ ፍብሪካዎቹን በማስፋፋትና ብዙ ሠራተኛ በመቅጠር ዳግም ብዙ ሸቀጣ ሸቀጥ በማምረት የምርት ሂደቱን ቀለበት መቀጠል ዘላቂ ልማትን ያመጣል፡፡ ለዚህ ነው፣ የውጭ ምንዛሪ ኩብለላ ለአንድ ሃገር እድገት ፀር ነው የምንለው፡፡ ያለ ውጭ ምንዛሪ ምንም ዓይነት ዓለም ዓቀፍ ግብይይት ማድረግ አንችልም እንደ ኢትዩጵያ ያሉ ደሃ ሃገራት ከግብርና ዘርፍ የሚገኝ ቡና፣ ጫት፣ሰሊጥ፣የቅባት እህሎች ወዘተ በውጭ ንግድ ተልኮ ከሁለት እስከ ሦስት ቢሊዩን ዶለር ይገኛል፡፡ ሃገራችን በገቢ ንግድ ከባህር ማዶ ሃገራት የምታስገባው ምርቶችና ሸቀጣ ሸቀጦች በትንሹ ከሰባት እስከ አስር ቢሊዩን ዶለር ይደርሳል፡፡ በዚህም የተነሳ የሃገራችን የንግድ ሚዛን በየዓመቱ ከአምስት እስከ ዘጠኝ ቢሊዩን ዶለር ኪሳራ ያሳያል፡፡ እንግዲህ በዚ ህ ላይ የውጭ ምንዛሪ ኩብለላ ሲታከልበት ዕጣ ፈንታችን ምን ይሆናል፡፡ እንደ ኒዲኩማናና ቦይስ በ2008 እኤአ ጥናት መሠረት ከሳህራ በታች ባሉ 40 ሃገራቶች በ2004እኤአ የውጭ ምንዛሪ ኩብለላ ከ420 እስከ 607 ቢሊዩን ዶለር ደርሶ እንደነበረና ሃገሮቹ ካለባቸው አጠቃላይ የውጭ ሃገር እዳ 398 ቢሊዩን ዶለር የውጭ ምንዛሪ ኩብለላ ከእጥፍ በላይ እንደነበር በጥናታቸው ተረጋግጦል፡፡ በዚህም አፍሪካ አሃጉር የዓለም ዋና ተበዳሪ እንድትሆን አድርጎታል፡፡ በተለይም በኢትዩጵያ የእውን የውጭ ምንዛሪ ኩብለላ ከ17 እስከ 23 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ክምችት በ2004እኤአ እንደነበረው ያሳያል፡፡ የተጣራ የውጭ ሃገራት ሃብት፤ ማለትም በ2004 እኤአ ወደ ውጭና ወደ ውስጥ የወጣኛ የገባ የውጭ ምንዛሪ ልዩነቶች 16 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ነበር፡፡ ይህም የውጭ ምንዛሪ ኩብለላ ከ አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት ሲነፃፀር 175 እጅ ከመቶ ይይዝ ነበር፡፡ ቀሪውን ከጥናቱ ምንጭ ያንብቡት፡፡

**"Capital Flight:-**Another potential source of mobilizing domestic resource, which can enhance domestic saving is stemming and reversing capital flight. Economic development is nothing but a process of investing, generating surplus and reinvesting that surplus for further improvement, expansion or new investment." (Ndikumana and Boyce 2008, p.35)…‹‹Specifically, for Ethiopia, the study has estimated the fact that the real capital flight for Ethiopia was about 17 Billion USA dollars, while the stock of capital flight as of 2004 was about 23 Billion dollars. The net foreign assets, which is the difference between outflow and inflow for the year 2004 was about 16 Billion dollars. Taking the capital/GDP ratio, it constitutes 175 per cent (Ndikumana and Boyce, 2008:41).Source: - Domestic resource mobilization in Sub-Saharan Africa: The case of Ethiopia by Tsegabirhan Weldegiorgis Abay, University of Addis Ababa, Ethiopia: Summer 2010

በአሁኑ ግዜ፤በዚህ የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኵብለላ ከሃገረ ኢትዩጵያ ወደ ባህር ማዶ ሃገራት የሚደረግ ዘረፋና ስርቆት ዋና ተዋናይ በመሆን የህወሃት/ኢህአዲግ ቱባ ባለስልጣኖች፣የጦር አበጋዞች ጀነራል መኮንኖች፣አንባሳደሮችና ዲፕሎማቶች፤ኢፈርትና ሜድሮክ ቢዝነስ ኩባንያዎች(የወርቅና የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኵብለላ) በማከናወን የአንበሳውን ድርሻ ሲቀራመቱ የቻይና ባለሃብቶችም ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በአሁኑ ሰዓት ከአስር በላይ የሚሆኑ የቻይና ባለሃብቶች ከ50 ሽህ እስከ 500000 ዩኤስ ዶለር ወደ ሃገራቸው ለማስወጣት ሲሞክሩ አዲስ አበባ ኤርፖርት ተይዘው ወህኒቤት ተፈርዶባቸው ይገኛሉ። የቻይና ባለሃብቶች ሦስት ቢሊዩን የኢትዩጵያ ብር በማከማቸት የእራሳቸው ስውር ካዝና የገንዘብ ዝውውር በማድረግ ከባንክ የውጭ ምንዛሪ ተመን በላይ በጥቁር ገበያውን በመቆጣጠር ብርን ወደ ዩኤስ ዶለር በመቀየር ወደ ቻይና በመላክ የሞቀ ንግድ ያከናውናሉ። እንዲሁም የክልል መንግስታት በተለይም ከኢትዩጵያ አጎራባች ሃገራት ጋር የሚዋሰኑ ክልሎች የአማራ፣ትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ጋምቤላ፣ቢኒሻንጉል ጉሙዝ፣ሱማሊያ ክልላዊ መንግስታት ድንበር በኩል የወርቅ፣ ቆዳ፣ ነዳጅና፣የቁም ከብት፣ የግብርና ምርቶች በተለይ ቡና፣ጫት፣ሰሊጥ፣ጤፍ የውጭ ምንዛሪና የንዋየ-ቅዱሳን ኵብለላ ወደ ጂቡቲ፣ ሱዳን፣ኬንያ፣ ሱማሊያና ኤርትራ በኩል በስፋት ይከናወናል።ከኢትዬጵያ የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኵብለላ ቀጣይነት በሃገሪቱ ኃብት አፍርቶ የመኖርና የመሬት የግል ኃብት ንብረትነት አለመዘዋወርና የህወሃት መንግስት የመሬት ሞኖፖሊ ፖሊሲ ዋነኛ ነቀርሳ መሆኑ የኢኮኖሚ ጠበብት ይስማሙበታል። ይሄ ፖሊሲ እስካልተቀየረ የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኵብለላ ማስቀረት ወረትና ዘበት ነው እንላለን።

### *5-ኢትዬጵያ* የባህር በር አልባ አገር **Ethiopia landlocked** developing **countries**

እንደ ተባበሩት መንግስታት ጥናት መሠረት የባህር በር አልባ አገራቶች በጣም ደሃ አገራቶች እንደሆኑ ተረጋግጦል። እነዚህ አገራት የባህር በር አልባ በመሆናቸው ከዓለም ዓቀፍ ንግድ ውድድር በትራንስፖርት ተጨማሪ ወጭ ምክንያት በንግድ ተወዳዳሪ ለመሆን አልቻሉም። በዚህም የተነሳ ከ31ዱ ሃገራት 16ቱ ዝቅተኛ ታዳጊ ሃገራቶች (least-developed countries (LDCs)) በመባል ይታወቃሉ። የሃገራቱ የመንገድና የባቡር መሰረተ ልማቶች አለማደግ፣ የትራንስፖርት ዘርፉ ወጭው በሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ እንዲንር ያደርገዋል። እንዲሁም የዕቃዎች መጎጎዥ ስነ ስርዓትና ደንብ አስተዳደር ደካማነት፣የሰለጠነ የተማረ የሰው ሃይል አለመኖር የንግዱን ዘርፍ ተሳታፊነት ያቀጭጨዋል። ሸቀጣ ሸቀጦች ከአንድም ሁለት ሃገራትን የባህር ወደቦች መተላለፍ ግድ ስለሚሆንባቸውና የሚላኩትና የሚመጡት እቃዎች ላይ ተጨማሪ ወጭ ያስከትላሉ። በተጨማሪም ቀልጣፋ የንግድ ልውውጥ ስርአት ያለመኖር እቃዎች በግዜው ባለመድረሳቸው ምክንያት ተጨማሪ ወጭ ያስከትላሉ።
ኤክስፖርት ለሚደረጉ ሸቀጣ ሸቀጦች የመጎጎዣና የኢንሹራንስ ወጭዎች ከፍተኛ መሆናቸው። የባህር በር የሌላቸው ሃገራት (12.9%) በመቶ፣ታዳጊ ሃገራት (8.1%) በመቶ፤ እንዲሁም ያደጉ ሃገራት(5.8%) በመቶ የኤክስፖርት ንግድ የመጎጎዣና የኢንሹራንስ ወጭ እንዳለባቸው በጥናት ተረጋግጦል። ለሃገሮች የኢኮኖሚ እድገት የሥነ-መልክዓ ምድር አቀማመጣቸው በተለይም የባህር በር ያላቸው ሃገራት ሸቀጣ ሸቀጦች ወደ ውጭ ኤክስፖርት ለመድረግና ወደ ሀገር ውስጥ ኢንፖርት ማድረግ በመቻላቸው ተጨማሪ የትራንስፖርት ወጭ ስለሌላቸው በአለም ዓቀፍ ንግድ ተወዳዳሪ መሆን ይቻላቸዋል፡አንደኛ የባህር በር አልባ ሃገራት ወደብ ባላቸው ሃገራት የመሠረተ ልማት ዘርፍ ላይ ጥገኞች ናቸው። ሁለተኛ በድንበር ሽግግር የፖለቲካ ግንኙነታቸው ላይ ጥገኛ ናቸው። ሦስተኛ በባህር በር ባላት ጎረቤት ሃገራት የሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት መኖር ጥገኛ ያረጋቸዋል። አራተኛ የጎረቤት ሃገር የንግድና አስተዳደር ችሎታ፣የንግድ ስርዓትና ደንብ እንዲሁም እውቀት ጥገኛ ያደርጋቸዋል። ቀልጣፋ ንግድ ልውውጥና አስተዳደር መኖር ለዓለም ዓቀፍ ንግድ ልውውጥ ወጭ በመቀነስ የባህር በር የሌላቸውን ሃገራት ተጠቃሚ ያደርጋል። ለማጠቃለል የሰለጠነ የወደብ አስተዳደር መኖር፣ቀረጥ/የጉምሩክ ድርጅት መኖር፣የአገልግሎት ሰጭ ዘርፎችና ጥሩ የመንገድ፣ የባቡርና የመርከብ አገልግሎቶችና ዘመናዊ መሠረተ ልማት መኖር እንዲሁም የሠለጠነ የቴሌኮምኒኬሽን ስልክ፣ ኢንተርኔት አገልግሎቶች መኖር የኤክስፖርትና ኢንፖርት ዓለም ዓቀፍ ንግድ ልውውጥ ቀልጣፋ በማድረግ ሁሉንም ተጠቃሚ ያደርጋል።
ሃገራችን ኢትዬጵያ የባህር በር የነበራት ወርቃማ ዘመን በ1991 እኤአ በኤርትራ የባህር በሯን አጣች። የአሰብ ወደብ ኢትዬጵያ የባህር በር ሆኖ ሊቀጥል የሚችልበትን ስምምነት ሕወሃት/ኢህአዲግ የሃገሪቶን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አሳልፎ በመስጠቱ የዛሬው ትውልድ ስርቶ መና፣ ነግዶ መና፣ ለመሆን በቅቶል። እስከ 1997 እኤአ ኢትዬጵያ በአሰብ ወደብ በኩል 75 በመቶ የንግድ ልውውጥ ዕቃዎች በማስገባትና በማስወጣት በወደቡ ትገለገል ነበር። በ1998 እኤአ በኢትዬጵያና ኤርትራ መኃል በተቀሰቀሰ ጦርነት ከ70 እስከ 100 ሽህ የሰው ህይወት የታጣበት ሻብያና ሕወሃት ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች በደም ባህር አጠቡት ደሀ ኢኮኖሜቸውም ወደመ። የሻብያና ሕወሃትየጦር አበጋዞች፣ ድንበር የተዘጋበትና የወደብ አገልግሎት ኢትዬጵያ ያጣችበት ዘመንና ሻብያም፣ወደብ ላይ የነበሩ እቃዎች የተወረሰበት ግዜና የኤርትራውያን ንብረቶችን በግፍ ሕወሃት የዘረፈበት ወቅት ነበር። በዚህም የተነሳ ኢትዬጵያ የጅቡቲን የባህር በር 781 ኪሎሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን ደካማ የወደብ አገልግሎትኛ ያልዘመነ የመሠረተ ልማት ዘርፍ ባለው ወደብ ለመገልገል ተገደደች። እንዲሁም ሃገሪቶ በኬንያና በሱማሌ ወደቦች ለመጠቀም ያልገለበጠችው ድንጋይ አልነበረም።
ኢትዬጵያ ጥሬ እቃዎች በማስወጣትና ግዙፍ የፖሮጀክት ግብዓቶች፣የቴክኖሎጂ ዕቃዎች፣ጦር መሳሪያዎች ወዘተ የመሳሰሉ ከፍተኛ ጭነቶች በጅቡቲ ወደብ 90 በመቶ ባህር ትራንስፖርት ዘርፍ በመጠቀም በየዓመቱ ከሦስት ቢሊዬን ዩኤስ ዶለር በላይ (60 ቢሊዬን ብር በአመት) ለጅቡቲ ወደብ ኪራይ ለመክፈል ተገዳለች። የሃገሪቱ የነዳጅ ፍጆታ ከሦስት ቢሊዬን ዩኤስ ዶለር በላይ ነው። ለማዳበሪያ መግዣ፣ለካፒታል ጉድስ መግዣ ለመኪኖች፣ ለባቡር፣ለአይሮፕላን፣ለጀነሬተሮች፣ ለተነርባኖች፣ለጦር መሣሪያዎች ታንክ፣ሚግ፣አዳፍኔ፣ ለህወሃት/ኢህአዴግ ሹማምንት 200 ቪኤይት ተገዝተው ወደብ ላይ ይገኛሉ። አረ ስንቱ! ይህ ነው እንቅልፍ የነሳኝ፣ከተማረው 100 ምሁራኖች 95ቱ የሃገራቸውን ኢኮኖሚ አያውቁም ከእራሴ ጭምር። የፖለቲካውን ታሪክ ግን ከመቶ መቶ ከኃምሳ ያውቃሉ። ስለ ሃገራችን ኢኮኖሚ ቪኦኤ፣ዶቸቬሎ፣ኢሣት፣ የተለያዩ ድረ-ገፆች የኢኮኖሚ ዐምድ የላቸውም!!! የባህር ማዶ ልሂቃን በእንግዚዘኛ ቋንቋ ከመሆኑ በስተቀር ይፅፋሉ ምስጋና ይድረሳቸው። ይህ ነው የአገራችን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ። ኢትዬጵያ የባህር በር አልባ አገር በመሆኖ ከግብርና ምርትና ሸቀጦችን ወደ ውጭ ሃገራት ሸጦ፣ የወደብ ኪራይ ለመክፈል የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ብቃት አይኖረውም፣ዓለም ተሸዓተ!!!። በሕወሃት/ኢህአዲግ መንግስት በአጠቃላይ የኢትዬጵያ ኢኮኖሚ ‹‹ምን ቢታለብ በገሌ!!!›› እንዳለችው ኢትዬጵያዊ ድመት ነው። በኢትዬጵያ ላለፍው አርባ ዐመታት፣የፖለቲካ ባህል ተደርጎ ከደርግ ዘመን ጀምሮ እስከ ሕወሃት ዘመን የተከወነ የፖለቲካ ስርዓት፡- የካድሬ፣ የኮሚሳሪያት፣የጓድ፣ የተገዳላይ፣የታጋይ፣የአርበኛ፣የፋኖ ወዘተ ስርዓት አክትሞ፣ የፖለቲካ ስልጣንና ከቴክኖክራት ስልጣን መለያየት ይኖርበታል። ቴክኖክራቶች በዩኒቨርሲቲዎች እውቀት ሰልጥነው በተመረቁ ሙያተኞች በነፃነት በትምህርትና እውቀት ደረጃ ተወዳድረው የጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ የሚኒስትርነት፣ የጀነራል መኮንንነት፣ የአንባሳደርነት፣የዩኒቨርሲቲ መምህራንነት፣ የመንግስታዊ ዘርፎችና ቢሮክራሲው ሠራተኛ በሙሉ በተማሩ ሰዎች መተካት አማራጭ የሌለው የልሂቃን አብዩት መገንባት አለበት። በዛም ነው የሃገሪቱ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ችግር፣ በተማሩት ዜጎች መፍትሄ የሚያገኘው። በካድሬዎች የፖለቲካ ስርዓተ መቃብር ላይ አዲሲቶ በምሁራን የተገነባች ኢትዬጵያ በነፃነት ታብባለች።በቋንቋና በዘር ላይ ያልተመሠረተ ክልላዊ አስተዳደሮች በጂኦ-ፖለቲካዊ መስፈርት በህዝብ ይሁንታ ይመሠረታል። አዲሲቶ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዬጵያ የህዝብ እንደራሴዎችና ተወካዩች የፓርላማ አባላት የተመረጡበትን ህዝብ የማስተዳደር ስልጣን ይኖራቸዋል። የዴሞክራሲና የፕሬስ ነፃነት በተማሩ እውቀት ባላቸው ጋዜጠኞችና ጦማሪያን ይሰራል። ህግ በህግ ባለሙያዎች፣ ህክምና በዶክተሮችና በነርሶች፣የመንገድ የህንፃ ግንባታ በማሃንዲሶች፣በአካውንቲንግ፣ በማኔጅመንት፣በፖለቲካ ስይንስ ወዘተ ይከናወናል።ፖለቲካ በባለሙያዎች ሥራ ጣልቃ አይግባ። ዘመኑ የዕውቀት ነው! ከዘመነ መሳፍንት! ወደ ዘመነ የብሄር ፓርቲ አበጋዞች! ብሎም ወደ ዘመነ ልሂቃን እንሸጋገር። ‹‹ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም!!!›› አበው ያሉት ለዚህ ነው።